# ከቁርኣንና ሐዲሥ የተውጣጡ ዱዓዎች

አዘጋጅ፡-

ከአላህ ከጃዪ ዶ/ር ሰዒድ ቢን ዐሊይ ቢን ወህፍ አልቀሕጧኒይ

شركاء التنفيذ:

دار الإسلام جمعية الربوة رواد الترجمة المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص.


Telephone: +966114454900

ceo@rabwah.sa

P.O.BOX: 29465

RIYADH: 11557

www.islamhouse.com

بسم الله الرحمن الرحيم

# ከቁርኣንና ሐዲሥ የተውጣጡ ዱዓዎች

﴿وَلِلَّهِ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰ فَٱدۡعُوهُ بِهَاۖ وَذَرُواْ ٱلَّذِينَ يُلۡحِدُونَ فِيٓ أَسۡمَٰٓئِهِۦۚ سَيُجۡزَوۡنَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ١٨٠﴾ [الأعراف: 180]

[1]{ለአላህም መልካም ስሞች አሉት። (ስትፀልዩ) በእርሷም ጥሩት። እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተዉዋቸው። ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይምመነዳሉ።}

---

[1] ሱረቱል አዕራፍ አንቀፅ : 180

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አላህ | አልአወል (የሁሉ መጀመሪያ) | አልአኺር (የሁሉም መጨረሻ) | አዝዟሂር (የሁሉ በላይ) | አልባጢን (እጅግ ቅርብ) |
| አልዐሊይ (እጅግ ከፍ ያለ) | አል አዕላ (ከሁሉም በላይ ከፍ ያለ) | አልሙተዓል (በችሎታና ኃያልነቱ ከፍ ያለ) | አልዐዚም (ትልቅ) | አልመጂድ (የውዳሴ ባለቤት) |
| አልከቢር (እጅግ ታላቅ) | አስሰሚዕ (ሁሉን ሰሚ) | አልበሲር (ሁሉን ተመልካች) | አልዐሊም (ሁሉን ዐዋቂ) | አልኸቢር (ውስጠ ዐዋቂ) |
| አልሐሚድ (በሁሉም የተመሰገነ) | አልዐዚዝ (ሁሉን አሸናፊ) | አለቀዲር (እጅግ ቻይ) | አልቃዲር (ሁሉን ቻይ) | አልሙቅተዲር (ሁሉን ነገር እጅግ በጣም ቻይ) |
| አልቀዊይ (ብርቱ) | አልመቲን (እጅግ ጠንካራ) | አልገኒይ (እጅግ የተብቃቃ) | አልሐኪም (እጅግ ጥበበኛ) | አልሐሊም (መቅጣት እየቻለ ታጋሽ) |
| አልዐፉው (እጅግ ይቅር ባይ) | አልገፉር (እጅግ መሀሪ) | አልገፋር (እጅግ በጣም መሀሪ) | አትተውዋብ (ፀፀት ተቀባይ) | አርረቂብ (የሁሉም ተጠባባቂ) |
| አሸሸሂድ (ግልፅም ስውርም የሚመለከት) | አልሐፊዝ (ሁሉንም ጠባቂ) | አልለጢፍ (ረቂቁንም ግዙፉንም አዋቂ) | አልቀሪብ (እጅግ ቅርብ) | አልሙጂብ (ተቀባይ) |
| አልወዱድ (ባሮቹን ወዳድ) | አሸሻኪር (ለባሮቹ መልካምነት እውቅና የሚሰጥ) | አሸሸኩር (ለባሮቹ ጥቂት ስራ ብዙ የሚመነዳ) | አስሰዪድ (የሁሉ አለቃ) | አስሶመድ (የሁሉ መጠጊያ) |
| አልቃሂር (ሁሉን አሸናፊ) | አልቀሃር (ሁሉንም እጅግ አሸናፊ) | አልቀሃር (ሁሉንም እጅግ አሸናፊ) | አልጀባር (ጉድለትን ጠጋኝና ኃያል የሆነ) | አልሐሲብ (ለተመኩበት በቂ) |
| አልሃዲ (ቀናውን መሪ) | አልሐከም (ዳኛ) | አልቁዱስ (ከእንከን የፀዳ) | አስሰላም (የሰላም ባለቤት) | አልበር (በጎ ዋይ) |
| አልወሃብ (ለጋሽ) | አርረሕማን (እጅግ በጣም አዛኝ) | አርረሒም (እጅግ በጣም ሩህሩህ) | አርራዚቅ (ሲሳይ ለጋሽ) | አርረዛቅ (ሲሳይን እጅግ ለጋሽ) |
| አልሐይ | አልከሪም | አልአክረም | አርረኡፍ (አዛኝ) | አልፈታሕ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **(ህያው)** | **(እጅግ ቸር)** | **(እጅግ በጣም ቸር)** | | **(መልካምን ሁሉ ከፋች)** |
| **አልቀይዩም (በራሱ የቆመ)** | **አርረብ (የሁሉ ጌታ)** | **አልመሊክ (የሁሉ ነገር ገዢ)** | **አልዋሒዱል አሐድ (አንድ የሆነ ብቸኛ)** | **አልሙተከቢር (ኩሩ)** |
| **አልኻሊቅ (የሁሉ ፈጣሪ)** | **አልኸላቅ (የእያንዳንዱ ቅንጣት ፈጣሪ)** | **አልባሪእ (ከኢምንት አስገኚ)** | **አልሙሶዊር (ቅርፅን አሳማሪ)አልሙእሚን (ደህንነትን ሰጪው)** | **አልሙሀይሚን (የበላይ ተቆጣጣሪው)** |
| **አልሙሒጥ (በእውቀት ሁሉን አካባቢ)** | **አልሙቂት (ባሮቹን ጠባቂ)** | **አልወኪል (የሁሉ ኋላፊ)** | **አልካፊ (ባሮቹን በቂ)** | **አልዋሲዕ (ወሰን አልባው)** |
| **አልሐቅ (እውነት የሆነ)** | **አልጀሚል (ውብ)** | **አርረፊቅ (ገር)** | **አልሐዪይ (ሓያእ የሚያደርግ)** | **አስሲቲር (የባሮቹን ጉድለት ሸፋኝ)** |
| **አልኢላህ (አምላክ)** | **አልቃቢድ (ሲሳይን በሚሻው ላይ የሚያጠብ)** | **አልባሲጥ (ሲሳይን የሚያሰፋ)** | **አልሙዕጢ (ሰጪ)** | **አልሙቀዲም (የሚያቀርብ)** |
| **አልሙአኺር (የሚያርቅ)** | **አልሙቢን (ማስረጃዎችን ግልፅ አድራጊ)** | **አልመናን (ለጋሽ)** | **አልወሊይ (ወዳጅ)** | **አልመውላ (አጋዥ)** |
| **አንነሲር (ረዳት)** | **አሽሻፊ (ፈዋሽ)** | **ማሊከልሙልክ (የንጉሶች ንጉስ)** | **ጃሚዑ-ንናስ (ሰዎችን ሰብሳቢ)** | **ኑሩ-ስሰማዋቲ ወልአርድ (የሰማያትና የምድር ብርሀን)** |
| **ዙልጀላሊ ወልኢክራም (የግርማና የመክበር ባለቤት)** | | **በዲዑ-ስሰማዋቲ ወልአርድ (ሰማያትና ምድርን ያለምንም የቀደመ ሞዴል ያስገኛቸው)[2]** | | |

---

[2] እነዚህን የአላህ ስሞች ከነቁርኣናዊ እና ሐዲሣዊ መረጃቸው (ሸርሕ አስማኢላሂ አልሁስና ፊ ደውኢል ኪታብ ወስሱና) በሚለው የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ሌላ መጽሐፍ ውስጥ ይመልከቱ!

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።

# መቅድም

ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው። እናመሰግነዋለን ፣ እገዛንም ከርሱ እንፈልጋለን፤ ምህረቱንም እንማፀነዋለን፤ ከነፍሳችን ክፋቶችና ከመጥፎ ስራችን በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራው ሰው አጥማሚ የለውም፤ ያጠመመውንም መሪ የለውም።ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ፤ ብቸኛና አጋርም እንደሌለው እመሰክራለሁ። ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልክተኛ እንደሆኑ እመሰክራለሁ። የአላህ ሰላት በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከፍርዱ ቀን በመልካም በተከተላቸውም ላይ ይስፈን። የአላህ የበዛ ሰላምም ይስፈንባቸው። ከዚህ በመቀጠል፡-

ይህ መጽሐፍ (አዝ

ዚክሩ ወድዱዓኡ ወልዒላጁ ቢርሩቃ ሚነልኪታቢ ወስሱናህ) ከሚለው መጽሐፌ የተቀነጨበ ነው።[3]በዚህ መጽሐፍ ውስጥ

---

[3] ከላይ የተጠቀሰው ዋቢ መጽሐፍ ለአላህ ምስጋና ይድረሰውና ውስጡ የሚገኙ ሐዲሦችን በሰፊው ምንጫቸውን ከመዘርዘር ጋር በአራት ቅፅ

ጠቀሜታው ቀለል እንዲል ብዬ የዱዓእን ክፍል ብቻ ቀንጭቤያለሁ። ሌሎችን ዱዓዎችና ጠቃሚ ፋይዳዎችንም እዚህ መጽሐፍ ላይ ጨምሬያለሁ። ኢን ሻአ አላሁ ተዓላየላቀውንና የተከበረውን አላህ በውብ ስሞቹና ከፍ ባሉ ባህሪያቶቹ እየተማፀንኩ ስራዬን ለተከበረው ፊቱ ጥርት ተደርጎ የተሰራ እንዲያደርገው እጠይቀዋለሁ። እሱ ለዚህ ረዳትና ቻይ ነውና።

የአላህ ሰላት፣ ሰላምና በረከት በነቢያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና ባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከፍርዱ ቀን በመልካም በተከተሏቸው ላይ ይስፈን።

**አዘጋጅ**

**ሰዕድ ቢን ዐሊይ ቢን ወህፍ አልቀሕጧኒይ**

**ጥንቅር በሸዕባን ወር 1408 ዓ·ሂ**

---

ታትሟል። አልአዝካር (ሒስኑል ሙስሊም) በመጀመሪያውና ሁለተኛው ቅፅ ፤ ዱዓእ በሶስተኛው ቅፅ ፤ ዒላጅ ቢርሩቃ በአራተኛው ቅፅ ይገኛሉ።

# የዱዓእ ትሩፋት

የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፡-

(وَقَالَ رَبُّكُمُ ادْعُونِي أَسْتَجِبْ لَكُمْ إِنَّ الَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِي سَيَدْخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ)

[4] {ጌታቻሁም አለ "ለምኑኝ እቀበላቹሀለውና ፤ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።"}

[5]የላቀውና የተከበረው አላህ እንዲህም ብሏል፡-

﴿وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌ ۖ أُجِيبُ دَعْوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ۖ فَلْيَسْتَجِيبُوا۟ لِى وَلْيُؤْمِنُوا۟ بِى لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴿١٨٦﴾﴾ [البقرة: 186]

{ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው) :- እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ። ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ ፤ በኔም ይመኑ ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና።}

---

[4] ሱረቱል ጓፊር:  አንቀፅ: 60

[5] ሱረቱል በቀራህ አንቀፅ: 186

ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል:- "ዱዓእ ራሱ አምልኮ ነው።"ጌታችሁ እንዲህ ብሏል፡-[6]፣ {ለምኑኝ እቀበላቹሀለውና}[7]ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል:-"ከፍ ያለውና የጠራው ጌታችሁ የሚያፍርና ቸር ነው። ባሪያው ለልመና ወደርሱ እጆቹን ከፍ አድርጎ ባዶ አድርጎ መመለስን ያፍራል። "ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህም ብለዋል: -"ወንጀልም ሆነ ዝምድና መቁረጥ የሌለበትን ልመና የሚለምን አንድም ሙስሊም የለም በዛች ልመና ምክንያት አላህ ከሶስት ነገሮች አንዱን የሚሰጠው ቢሆን እንጂ: ወይ የለመነው በፍጥነት ይሰጠዋል ፤ ወይ ልመናው ለመጪው ዓለም መልካም ምንዳ ማደለቢያ ይሆንለታል ፤ ወይ የለመነውን አቻ መጥፎ ነገር ከሱ ዞር ያስደርግለታል። " ሶሀቦችም " ስለዚህ (ዱዓእ) እናብዛ?" አሉ። እሳቸውም "(ዱዓእ ካበዛችሁ) የአላህ ስጦታም እጅግ የበዛ ነው።" አሏቸው።"

---

[6] ቲርሚዚይ በ5/566ና 5/462 የሐዲሥ ቁ, 3573 ፣ አሕመድ በ3/18 የሐዲሥ ቁ, 11150 ዘግበውታል። አልባኒይ በሶሒሕ አልጃሚዑ አስሶኚር 5/116ና በሶሒሕ ሱነን አትቲርሚዚይ 3/140 መጽሐፍታቸው ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[7] የመጽሐፉን መሰረት ቅፅ 3/ ከገፅ 863 - 926 ተመልከት።

የዱዓእ ሡነ-ሥርአት እና ተቀባይነትን የሚያስገኙ ምክንያቶች[8]

1- ለአላህ ብቻ አጥርቶ (በኢኽላስ) መለመን፤

2- አላህን በማመስገንና እርሱን በማወደስ ቀጥሎም በነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ ሰለዋት በማውረድ መጀመር። ሲያጠናቅቁም በዚሁ መልክ ማጠናቀቅ፤

3- ዱዐችን ሲያደርጉ ቁርጠኛ መሆንና ተቀባይነት እንደሚያገኝ እርግጠኛ መሆን፤

4- ዱዓእ ስናደርግ ችክ ብለን አዘውትረን ማድረግና አለመቻኮል፤

5- ልብን በዱዓዉ ላይ መጣድ (ሀሳብን መሰብሰብ)፤

6- በድሎትም ሆነ በችግር ወቅት ዱዓእ ማድረግ፤

7- ከአላህ በስተቀር ማንንም አይለመንም፤

---

[8] እነዚህን ሡነ-ሥርአቶችና ተቀባይነትን የሚያስገኙ ምክንያቶችን ከነማስረጃቸው ከዋናው መጽሐፍ ቅፅ 3 ከገፅ 927 - 975 ይመልከቱ።

8- በቤተሰቦች፣ በገንዘብ፣ በልጅና በነፍስ ላይ (መጥፎን) አለመለመን ፤

9- በዝግታና በከፍታ መሀል በሆነ መልኩ ማድረግ፤ ዱዓእ ስናደርግ ድምፅን ዝቅ ማድረግ፤

10- ወንጀልን ማመንና ለሱ ምህረት መጠየቅ፤ ፀጋን ማመንና በርሱ ላይ አላህን ማመስገን፤

11- ዱዓእ ስናደርግ ቃላትን ለማስዋብ አለመጨነቅ፤

12- በመዋደቅ፣ በመተናነስ፣ በክጃሎትና በፍርሀት መካከል ሆኖ ዱዓእ ማድረግ፤

13- ከተውበት ጋር የበደልነውን መመለስ፤

14- ሶስት ሶስት ጊዜ ዱዓእ ማድረግ፤

15- ወደ ቂብላ ዞሮ ማድረግ፤

16- በዱዓእ ወቅት እጆችን ከፍ ማድረግ፤

17- ከተቻለ ከዱዓእ በፊት ዉዱእ ማድረግ፤

18- በዱዓእ ወሰን አለማለፍ፤

19- ለሌላም ሰው ዱዓእ የሚያደርጉ ከሆነ ቅድሚያ ለራስ በማድረግ መጀመር ፤[9]

20- የአላህን ውብ ስሞችና የላቁ ባህሪያቶቹን ወይም ዱዓእ አድራጊው ራሱ የሠራቸውን መልካም ሥራዎች ወይም በህይወት ባለና አቅራቢያው ባለ መልካም ሰው ዱዓእ ወደ አሏህ መቃረብ፤

21- ምግቡ፣ መጠጡ እና አልባሳቱ ከሐላል መሆናቸው ፤

22- በወንጀል ወይም ዝምድናን በመቁረጥ አለመለመን ፤

23- በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል ይገባል፤

24- ከሁሉም ወንጀሎች መራቅ፤

---

[9] በርግጥ ከነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዱዓእ ሲያደርጉ ከራሳቸው መጀመራቸውም ተገኝቷል ልክ እንደዚሁ ከራሳቸው ሳይጀምሩ ሌላውን ያስቀደሙበትም አጋጣሚ አለ፤ ለአነስ፣ ለኢብኑ ዓባስ ፣ ለኡሙ ኢስማዒልና ለሌሎችም ዱዓእ ያደረጉበትን አጋጣሚ ይመስል። በዚህ ነጥብ ዙሪያ ዝርዝሩን ኢማሙ ነወዊይ ሶሒሕ ሙስሊምን ባብራሩበት መጽሐፍ ቅፅ 15 /144 ገፅ፣ በቱሕፈቱል አሕወዚይ ሸርሕ ሱነን አትቲርሚዚይ ቅፅ 9/ 328 ገፅና በፈትሑል ባሪ ሸርሕ ሶሒሕ አልቡኻሪይ ቅፅ 1/ ገፅ 281 ይመልከቱ።

ዱዓእ ተቀባይነት የሚያገኙበት ጊዜዎች፣ ሁኔታዎችና ስፍራዎች[10]

1- የመወሰኛይቱ ሌሊት (ለይለቱል ቀድር) ላይ

2- የመጨረሻው የሌሊት ክፍል ላይ

3- ከግዴታ ሶላቶች በኋላ

4- በአዛንና ኢቃማህ መካከል

5- በሁሉም የምሽቱ ክፍል የተወሰነ ሰዓት

6- ለግዴታ ሶላት አዛን በሚባል ወቅት

7- ዝናብ በሚወርድበት ወቅት

8- በአላህ መንገድ የተሰለፉ ሰልፎች በጦርነት በተጨናነቁ ወቅት

9- ከጁሙዓ ቀን የተወሰነ ሰዓት

ከጁሙዓ ቀን ዱዓ ተቀባይነት የሚያገኝበትን ወቅት በተመለከተ ሚዛን የሚደፋው አቋም የጁሙዐ ቀን የዐስር

---

[10] እነዚህን ወቅቶች፣ ሁኔታዎችና ስፍራዎች ከነማስረጃቸው በዝርዝር ዋናው መጽሐፍ ውስጥ 3/975-1117 ይመልከቱ።

የመጨረሻው ወቅት ላይ የሚለው ነው። በርግጥ ኹጥባ በሚደረግበትና ሶላቱ በሚሰገድበት ወቅትም ሊሆን ይችላል።

10- የዘምዘም ውኃን በሚጠጡበት ወቅት ከእውነተኛ ኒያ ጋር ዱዓእ ማድረግ

11- በሱጁድ ውስጥ

12- በምሽት ከእንቅልፍ በሚነቁ ጊዜ፤ በዚህ ወቅት እንዲባል የመጣውን ዱዓእ ማድረግ

13- በውዱእ ተኝቶ ከዚያም በሌሊት ሲነቃ ዱዓእ ካደረገ፤

14- (ላ ኢላሀ ኢላ አንተ ሱብሐነከ ኢኒ ኩንቱ ሚነዝዟሊሚን) በሚለው ውዳሴ ዱዓእ በምናደርግበት ወቅት

15- ሰዎች የሟችን ህልፈት ተከትሎ የሚያደርጉት ዱዓእ

16- በመጨረሻው ተሸሁድ ወቅት አላህ ላይ ካወደስንና በነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ ሶለዋት ካወረድን በኋላ ዱዓእ ማድረግ።

17 አላህን ከተለመነበት የሚቀበለው ከተጠየቀበትም የሚሰጥበት በሆነው ታላቅ ስሙ ዱዓእ በምናደርግ ጊዜ[11]።

18 - አንድ ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ በሌለበት የሚያደርገው ዱዓእ፤

19 - የዐረፋህ ቀን በዐረፋህ ስፍራ የሚደረግ ዱዓእ፤

20 - በረመዳን ወር ውስጥ የሚደረግ ዱዓእ፤

21 - በመተዋወሻ (መማማሪያ) ስፍራዎች ሙስሊሞች ለመተዋወስ በተሰባሰቡበት ጊዜ የሚደረግ ዱዓእ፤

22 - በመከራ ወቅት "ኢና ሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን፤ አላሁምመ አጁርኒ ፊ ሙሲበቲ ፤ ወኽሉፍ ሊ ኸይረን ሚንሃ" በማለት ዱዓእ ስናደርግ፤ ትርጉሙም (እኛ የአላህ ነን ወደ አላህም ተመላሾች ነን፤ አላህ ሆይ በመከራዬ ምንዳን ስጠኝ፤ ከርሱ የተሻለንም መልካም ለኔ ተካልኝ) ማለት ነው።

23 - ልብን ወደ አላህ ባዞርንና ኢኽላሳችን በበረታ ወቅት የሚደረግ ዱዓእ፤

---

[11] የአላህን እጅግ ታላቅ ስም በተመለከተ እዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሐዲሥ ቁጥር 203 ፣ በቁጥር 104 እና 105 ላይ ይመልከቱ።

24 - ተበዳይ በበዳይ ላይ የሚያደርገው ዱዓእ፤

25 - ወላጅ ለልጁ የሚያደርገውም በልጁ ላይ የሚያደርገውም ዱዓእ፤

26 - ጉዞ የወጣ ሰው የሚያደርገው ዱዓእ፤

27 - ፆመኛ እስኪያፈጥር ድረስ የሚያደርገው ዱዓእ፤

28 - ፆመኛ በሚያፈጥር ጊዜ የሚያደርገው ዱዓእ፤

29 - የተቸገረ ሰው የሚያደርገው ዱዓእ፤

30 - የፍትሀዊ መሪ ዱዓእ፤

31 - መልካም ልጅ ለወላጆቹ የሚያደርገው ዱዓእ፤

32 - ከዉዱእ በኋላ በሐዲሥ የመጣውን ዱዓእ ማድረግ፤

33 - በሐጅ ወቅት በትንሹ የመወርወሪያ ስፍራ (ጀምረቲ አስ ሱግራ) ከወረወሩ በኋላ የሚደረግ ዱዓእ፤

34 - በሐጅ ወቅት በመሀከለኛው የመወርወሪያ ስፍራ (ጀምረቲ አል ዉስጧ) ከወረወሩም በኋላ የሚደረግ ዱዓእ፤

35 - ካዕባ ውስጥ የሚደረግ ዱዓእ፣ እንዲሁም የካዕባ አንድ አካል ነውና ሒጅር ውስጥ የሰገደም ሰው የሚያደርገው ዱዓእ፤

36 - አስ'ሰፋ ላይ ተቁሞ የሚደረግ ዱዓእ፤

37 - መርዋህ ላይ ተቁሞ የሚደረግ ዱዓእ፤

38 - መሽዐረል ሐራም ዘንድ (ሙዝደሊፋ ላይ የሚገኝ ተራራ ነው።) የሚደረግ ዱዓእ፤

አንድ አማኝ የትም ስፍራ ሆኖ ዘውትር ጌታውን ይለምናል። የተከበረውና የላቀው አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِى عَنِّى فَإِنِّى قَرِيبٌ ۖ أُجِيبُ دَعْوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ۖ فَلْيَسْتَجِيبُوا۟ لِى وَلْيُؤْمِنُوا۟ بِى لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴿١٨٦﴾﴾ [البقرة: 186]

[12] {ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው) :- እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ። ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ ፤ በኔም ይመኑ ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና። } ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ወቅቶች፣ ሁኔታዎችና ስፍራዎች ተጨማሪ ትኩረት ስለተሰጣቸው ይለያሉ።

---

[12] ሱረቱል በቀራህ፤ አንቀፅ ፡ 186

# ከቁርኣንና ሐዲሥ የተውጣጡ ዱዓዎች

ምስጋና ብቸኛ ለሆነው ለአላህ የተገባ ነው፤ የአላህ ሰላትና ሰላም ከርሳቸው በኋላ ነቢይ በሌለው ላይ ይስፈን።

﴿بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ١ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ٣ مَٰلِكِ يَوۡمِ ٱلدِّينِ ٤ إِيَّاكَ نَعۡبُدُ وَإِيَّاكَ نَسۡتَعِينُ ٥ ٱهۡدِنَا ٱلصِّرَٰطَ ٱلۡمُسۡتَقِيمَ ٦ صِرَٰطَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمۡتَ عَلَيۡهِمۡ غَيۡرِ ٱلۡمَغۡضُوبِ عَلَيۡهِمۡ وَلَا ٱلضَّآلِّينَ ٧﴾ [الفاتحة: 1-7]

1 - (ትርጉሙ: በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፤ * (ምስጋና ለአላህ ይገባው የአለማት ጌታ ለሆነው ፤ * (እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ ፤ * (የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው ፤ * (አንተን ብቻ እንገዛለን ፤ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን። * (ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። *(የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)።)[13].

﴿...رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧﴾ [البقرة: 127]

---

[13] ሱረቱል ፋቲሓህ አንቀፅ 1 - 7

2 -(ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ከእኛ ተቀበል። አንተ ሰሚውና አዋቂው አንተ ነህና።})[14].

﴿رَبَّنَا وَٱجۡعَلۡنَا مُسۡلِمَيۡنِ لَكَ وَمِن ذُرِّيَّتِنَآ أُمَّةٗ مُّسۡلِمَةٗ لَّكَ وَأَرِنَا مَنَاسِكَنَا وَتُبۡ عَلَيۡنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ١٢٨﴾ [البقرة: 128]

3 - (ትርጉሙ: {በኛም ላይ ተመለስልን ፤ አንተ ፀፀትን ተቀባዩ ሩህሩህ አንተ ብቻ ነህና።})[15].

﴿... رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِي ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٗ وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِ حَسَنَةٗ وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ٢٠١﴾ [البقرة: 201]

4 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን ፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን።})[16].

﴿... سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ غُفۡرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ٢٨٥﴾ [البقرة: 285]

---

[14] ሱረቱል በቀራህ፤  አንቀፅ: 127

[15] ሱረቱል በቀራህ፤ አንቀፅ: 128

[16] ሱረቱል በቀራ፤  አንቀፅ:  201

5 - (ትርጉሙ: {ሰማን ታዘዝንም። ጌታችን ሆይ! ምህረትህን (እንሻለን)። መመለሻም ወዳንተ ብቻ ነው።})[17].

﴿... رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذۡنَآ إِن نَّسِينَآ أَوۡ أَخۡطَأۡنَاۚ رَبَّنَا وَلَا تَحۡمِلۡ عَلَيۡنَآ إِصۡرٗا كَمَا حَمَلۡتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِنَاۚ رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلۡنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦۖ وَٱعۡفُ عَنَّا وَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَآۚ أَنتَ مَوۡلَىٰنَا فَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ٢٨٦﴾ [البقرة: 286]

6 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንስት አትያዘን፤ (አትቅጣን)። ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ላይ እንደጫንከው በእኛ ላይ አትጫንብን። ጌታችን ሆይ! ለኛም በርሱ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን። ከእኛም ይቅርታ አድርግ ለእኛም ምህረት አድርግ። እዘንልንም፤ ዋቢያችን አንተ ነህና። በከሀዲዎች ህዝቦች ላይ እርዳን።})[18].

﴿رَبَّنَا لَا تُزِغۡ قُلُوبَنَا بَعۡدَ إِذۡ هَدَيۡتَنَا وَهَبۡ لَنَا مِن لَّدُنكَ رَحۡمَةًۚ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡوَهَّابُ ٨﴾ [آل عمران: 8]

---

[17] ሱረቱል በቀራህ፤ አንቀፅ: 285

[18] ሱረቱል በቀራህ፤ አንቀፅ: 286

7 - (ትርጉሙ: {(እነሱም ይላሉ) "ጌታችን ሆይ! ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኋላ ልቦቻችንን አታዘንብልብን። ከአንተ ዘንድ የሆነን ችሮታም ለኛ ስጠን። አንተ በጣም ለጋስ ነህና። })[19].

﴿... رَبَّنَآ إِنَّنَآ ءَامَنَّا فَٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ﴾ [آل عمران: 16]

8 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! እኛ አመንን ኃጢአቶቻችንንም ለእኛ ማር፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን።})[20].

﴿... رَبِّ هَبۡ لِي مِن لَّدُنكَ ذُرِّيَّةً طَيِّبَةًۖ إِنَّكَ سَمِيعُ ٱلدُّعَآءِ﴾ [آل عمران: 38]

9 - (ትርጉሙ: {ጌታዬ ሆይ! ከአንተ ዘንድ መልካም ዘርን ለኔ ስጠኝ አንተ ፀሎትን ሰሚ ነህና።})[21].

---

[19] ሱረቱ አሊ ዒምራን፤ አንቀፅ: 8

[20] ሱረቱ ኣሊ ዒምራን: 16

[21] ሱረቱ ኣሊ ዒምራን ፤ አንቀፅ: 38

﴿رَبَّنَآ ءَامَنَّا بِمَآ أَنزَلۡتَ وَٱتَّبَعۡنَا ٱلرَّسُولَ فَٱكۡتُبۡنَا مَعَ ٱلشَّٰهِدِينَ٥٣﴾ [آل عمران: 53]

10 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ባወረድከው አመንን፤ መልክተኛውንም ተከተልን ፤ ከመስካሪዎችም ጋር መዝግበን})[22].

﴿وَمَا كَانَ قَوۡلَهُمۡ إِلَّآ أَن قَالُواْ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَإِسۡرَافَنَا فِيٓ أَمۡرِنَا وَثَبِّتۡ أَقۡدَامَنَا وَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ١٤٧﴾ [آل عمران: 147]

11 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንንና በነገራችን ሁሉ ወሰን ማለፋችንን ለእኛ ማር ፤ ይዞታችንንም አደላድል ፤ በከሀዲዎች ህዝቦች ላይም እርዳን።})[23].

﴿... رَبَّنَا مَا خَلَقۡتَ هَٰذَا بَٰطِلٗا سُبۡحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٩١ رَبَّنَآ إِنَّكَ مَن تُدۡخِلِ ٱلنَّارَ فَقَدۡ أَخۡزَيۡتَهُۥۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ١٩٢ رَّبَّنَآ إِنَّنَا سَمِعۡنَا مُنَادِيٗا يُنَادِي لِلۡإِيمَٰنِ أَنۡ ءَامِنُواْ بِرَبِّكُمۡ فَـَٔامَنَّاۚ رَبَّنَا فَٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرۡ

---

[22] ሱረቱ ኣሊ ዒምራን፤ አንቀፅ: 53

[23] ሱረቱ አሊ ዒምራን፤ አንቀፅ: 147

عَنَّا سَيِّـَٔاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ ٱلۡأَبۡرَارِ ١٩٣ رَبَّنَا وَءَاتِنَا مَا وَعَدتَّنَا عَلَىٰ رُسُلِكَ وَلَا تُخۡزِنَا
يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۖ إِنَّكَ لَا تُخۡلِفُ ٱلۡمِيعَادَ ١٩٤﴾ [آل عمران: 191-194]

12 -(ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ይኽን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ ጥራት ይገባህ፤ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን። ጌታችን ሆይ! አንተ እሳት የምታገባውን ሰው በእርግጥ አዋረድከው፤ ለበደለኞችም ምንም ረዳቶች የሉዋቸውም። ጌታችን ሆይ! እኛ በጌታችሁ እመኑ በማለት ወደ እምነት የሚጠራን ጠሪ ሰማን። አመንም። ጌታችን ሆይ! ሀጢአቶቻችንንም ለኛ ማር። ክፉ ስራዎቻችንንም ከኛ አብስ። ከንፁሆቹም ሰዎች ጋር ግደለን፤ጌታችን ሆይ! በመልክተኞችህም ላይ ተስፋ ቃል ያደረግክልንን ስጠን። በትንሳኤ ቀንም አታዋርደን። አንተ ቀጠሮን አታፈርስምና።})[24].

﴿... رَبَّنَآ ءَامَنَّا فَٱكۡتُبۡنَا مَعَ ٱلشَّٰهِدِينَ ٨٣﴾ [المائدة: 83]

13 -(ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! አመንን ከመስካሪዎችም ጋር ፃፈን ።})[25].

---

[24] ሱረቱ ኣሊ ዒምራን፤ ከአንቀፅ: 191 - 194

[25] ሱረቱ አልማኢዳህ፤ አንቀፅ: 83

﴿... رَبَّنَا ظَلَمۡنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمۡ تَغۡفِرۡ لَنَا وَتَرۡحَمۡنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ٢٣﴾ [الأعراف: 23]

14 -(ትርጉም: {ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን። ለእኛ ባትምር ባታዝንልንምበእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን።})[26].

﴿...۞رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا مَعَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ٤٧﴾ [الأعراف: 47]

15 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ከበደለኞች ጋር አታድርገን። })[27].

﴿... أَنتَ وَلِيُّنَا فَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَاۖ وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡغَٰفِرِينَ ١٥٥ ۞ وَٱكۡتُبۡ لَنَا فِي هَٰذِهِ ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٗ وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِ ...١٥٦﴾ [الأعراف: 155-156]

16 - አላህ ሆይ! (ትርጉሙ: {አንተ ረዳታችን ነህና ለእኛ ምህረት አድርግልን። እዘንልንም። አንተም ከመሀሪዎች ሁሉ በላጭ ነህ።ለእኛም በዚች በቅርቢቱ ዓለም መልካሟን በመጨረሻይቱም (መልካሟን) ፃፍልን።})[28].

---

[26] ሱረቱ አልአዕራፍ፤ አንቀፅ: 23

[27] ሱረቱ አልአዕራፍ፤ አንቀፅ: 47

[28] ሱረቱ አልአዕራፍ፤ ከአንቀፅ 155 - 156

﴿... حَسۡبِيَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُۖ وَهُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡعَظِيمِ﴾ [التوبة: 129]

17 - (ትርጉሙ: {አላህ በቂዬ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። በእርሱ ላይ ተጠጋሁ እርሱም የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው በላቸው።})[29].

﴿... رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا فِتۡنَةٗ لِّلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ۝٨٥ وَنَجِّنَا بِرَحۡمَتِكَ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ۝٨٦﴾ [يونس: 85-86]

18 - (ትርጉሙ: {ጌታችን ሆይ! ለበደለኞች ህዝቦች መፈተኛ አታድርገን። በእዝነትህም ከከሀዲዎች ህዝቦች አድነን።})[30].

﴿... رَبِّ إِنِّيٓ أَعُوذُ بِكَ أَنۡ أَسۡـَٔلَكَ مَا لَيۡسَ لِي بِهِۦ عِلۡمٞۖ وَإِلَّا تَغۡفِرۡ لِي وَتَرۡحَمۡنِيٓ أَكُن مِّنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ۝٤٧﴾ [هود: 47]

19 - (ትርጉሙ: {ጌታዬ ሆይ! በእርሱ ለእኔ እውቀት የሌለኝን ነገር የምጠይቅህ ከመሆን እኔ ባንተ እጠበቃለሁ። ለእኔም ባትምረኝና ባታዝንልኝ ከከሳሪዎቹ እሆናለሁ።})[31].

---

[29] ሱረቱ አትተውባህ፤ አንቀፅ: 129

[30] ሱረቱ ዩኑስ፤ ከአንቀፅ 85 - 86

﴿...ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ أَنتَ وَلِيِّۦ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ تَوَفَّنِي مُسۡلِمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّٰلِحِينَ ١٠١﴾ [يوسف: 101]

20 - አላህ ሆይ! (ትርጉሙ: {የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ! አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ። ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ። በመልካሞቹም አስጠጋኝ።})[32]

﴿ رَبِّ ٱجۡعَلۡ هَٰذَا ٱلۡبَلَدَ ءَامِنٗا وَٱجۡنُبۡنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعۡبُدَ ٱلۡأَصۡنَامَ ٣٥﴾ [إبراهيم: 35]

21 - (ትርጉሙ: {ጌታዬ ሆይ! ይህንን ሀገር (መካን) ጸጥተኛ አድርገው እኔንም ልጆቼንም ጣኦታትን ከመገዛት አርቀን።})[33].

﴿رَبِّ ٱجۡعَلۡنِي مُقِيمَ ٱلصَّلَوٰةِ وَمِن ذُرِّيَّتِيۚ رَبَّنَا وَتَقَبَّلۡ دُعَآءِ ٤٠﴾ [إبراهيم: 40]

---

[31] ሱረቱ ሁድ፤ አንቀፅ: 47

[32] ሱረቱ ዩሱፍ፤ አንቀፅ 101 ፤ ለተጨማሪ ፋይዳዎች የኢብኑል ቀይም (አልፈዋኢድ) መጽሐፍን ገፅ 436 እና 437 ይመልከቱ።

[33] ሱረቱ ኢብራሂም፤ አንቀፅ: 35

22 - {ጌታዬ ሆይ! ሶላትን አዘውትሬ የምሰግድ አድርገኝ። ከዘሮቼም (አድርግ)። ጌታችን ሆይ! ጸሎቴንም ተቀበለኝ።}[34].

﴿رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لِي وَلِوَٰلِدَيَّ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلۡحِسَابُ۝٤١﴾ [إبراهيم: 41]

23 - {ጌታችን ሆይ! ለእኔም ለወላጆቼም ለምእመናንም ሁሉ ምርመራ በሚደረግበት ቀን ማር።}[35].

﴿... رَبَّنَآ ءَاتِنَا مِن لَّدُنكَ رَحۡمَةٗ وَهَيِّئۡ لَنَا مِنۡ أَمۡرِنَا رَشَدٗا۝١٠﴾ [الكهف: 10]

24 - {ጌታችን ሆይ! ከአንተ ዘንድ እዝነትን ስጠን፤ ለእኛም ከነገራችን ቅንን አዘጋጅልን።}[36].

﴿قَالَ رَبِّ ٱشۡرَحۡ لِي صَدۡرِي۝٢٥ وَيَسِّرۡ لِيٓ أَمۡرِي۝٢٦ وَٱحۡلُلۡ عُقۡدَةٗ مِّن لِّسَانِي۝٢٧ يَفۡقَهُواْ قَوۡلِي۝٢٨﴾ [طه: 25-28]

---

[34] ሱረቱ ኢብራሂም፤ አንቀፅ: 40

[35] ሱረቱ ኢብራሂም፤ አንቀጽ: 41

[36] ሱረቱል ከህፍ፤ አንቀፅ: 10

25 - {ጌታዬ ሆይ! ልቤን አስፋልኝ። ነገሬንም ለእኔ አግራልኝ። ከምላሴም መኮላተፍን ፍታልኝ። ንግግሬን ያውቃሉና።}[37].

﴿... رَّبِّ زِدۡنِي عِلۡمٗا ١١٤﴾ [طه: 114]

26 - {ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ።}[38].

﴿.... لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبۡحَٰنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ٨٧﴾ [الأنبياء: 87]

27 - {ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ጥራት ይገባህ። እኔ በእርግጥ ከበዳዮች ነበርኩ።}[39].

﴿وَزَكَرِيَّآ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ رَبِّ لَا تَذَرۡنِي فَرۡدٗا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٨٩﴾ [الأنبياء: 89]

28 - {ጌታዬ ሆይ! ብቻዬን አትተወኝ። አንተም ከወራሾች ሁሉ በላጭ ነህ።}[40].

---

[37] ሱረቱ ጣሀ፤ ከአንቀፅ 25 - 28

[38] ሱረቱ ጣሀ፤ አንቀፅ: 114

[39] ሱረቱል አንቢያእ፤ አንቀፅ 87

[40] ሱረቱል አንቢያእ፤ አንቀፅ: 89

﴿وَقُل رَّبِّ أَعُوذُ بِكَ مِنۡ هَمَزَٰتِ ٱلشَّيَٰطِينِ ۝٩٧ وَأَعُوذُ بِكَ رَبِّ أَن يَحۡضُرُونِ ۝٩٨﴾ [المؤمنون: 97-98]

29 - {ጌታዬ ሆይ! ከሰይጣናት ጉትጎታዎች በአንተ እጠበቃለሁ። በንተም ጌታዬ ሆይ! (በነገሮቼ) ወደእኔ ከመጣዳቸው እጠበቃለሁ።}[41].

﴿... رَبَّنَآ ءَامَنَّا فَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلرَّٰحِمِينَ ۝١٠٩﴾ [المؤمنون: 109]

30 - {ጌታችን ሆይ! አምነናልና ማረን። እዘንልንም አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ።}[42].

﴿... رَبَّنَا ٱصۡرِفۡ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَۖ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا ۝٦٥﴾ [الفرقان: 65]

31 - {ጌታዬ ሆይ! ማር እዘንም። አንተም ከአዛኞች ሁሉ በላጭ ነህ።}[43].

---

[41] ሱረቱል ሙእሚኑን፤ ከአንቀፅ 97 - 98

[42] ሱረቱል ሙእሚኑን፤ አንቀፅ: 109

[43] ሱረቱል ሙእሚኑን፤ አንቀፅ: 118

﴿إِنَّهَا سَآءَتۡ مُسۡتَقَرّٗا وَمُقَامٗا ٦٦﴾ [الفرقان: 66]

32 - {ጌታችን ሆይ! የገሀነምን ቅጣት ከእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የማይለቅ ነውና።* እርሷ መርጊያና መቀመጫ በመሆን ከፋች።}[44].

﴿... رَبَّنَا هَبۡ لَنَا مِنۡ أَزۡوَٰجِنَا وَذُرِّيَّٰتِنَا قُرَّةَ أَعۡيُنٖ وَٱجۡعَلۡنَا لِلۡمُتَّقِينَ إِمَامًا ٧٤﴾ [الفرقان: 74]

33 - {ጌታችን ሆይ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ለዓይኖች መርጊያን ለእኛ ስጠን። አላህን ለሚፈሩትም መሪ አድርገን።}[45].

﴿رَبِّ هَبۡ لِي حُكۡمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّٰلِحِينَ ٨٣ وَٱجۡعَل لِّي لِسَانَ صِدۡقٖ فِي ٱلۡأٓخِرِينَ ٨٤ وَٱجۡعَلۡنِي مِن وَرَثَةِ جَنَّةِ ٱلنَّعِيمِ ٨٥﴾ [الشعراء: 83-85]

34 -{ጌታዬ ሆይ! እውቀትን ስጠኝ! በደጋጎቹም ሰዎች አስጠጋኝ። በኋለኞቹም ህዝቦች ውስጥ ለእኔ መልካም ዝናን አድርግልኝ። የጸጋይቱን ጀነት ከሚወርሱትም አድርገኝ።}[46].

---

[44] ሱረቱል ፉርቃን፤ ከአንቀፅ 65 - 66

[45] ሱረቱል ፉርቃን፤ አንቀፅ: 84

[46] ሱረቱ አሽሹዐራእ፤ ከአንቀፅ 83 - 85

﴿وَلَا تُخۡزِنِي يَوۡمَ يُبۡعَثُونَ ٨٧ يَوۡمَ لَا يَنفَعُ مَالٞ وَلَا بَنُونَ ٨٨ إِلَّا مَنۡ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلۡبٖ سَلِيمٖ ٨٩﴾ [الشعراء: 87-89]

35 - {በሚቀሰቀሱበት ቀንም አታዋርደኝ * ገንዘብም ልጆችም በማይጠቅሙበት ቀን። ወደ አላህ በንፁህ ልብ የመጣ ሰው ቢሆን እንጂ።}[47].

﴿... رَبِّ أَوۡزِعۡنِيٓ أَنۡ أَشۡكُرَ نِعۡمَتَكَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتَ عَلَيَّ وَعَلَىٰ وَٰلِدَيَّ وَأَنۡ أَعۡمَلَ صَٰلِحٗا تَرۡضَىٰهُ وَأَدۡخِلۡنِي بِرَحۡمَتِكَ فِي عِبَادِكَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١٩﴾ [النمل: 19]

36 - {ጌታዬ ሆይ! ያቺን በእኔና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም በጎ ስራ እንድሰራ ምራኝ። በችሮታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አስገባኝ። }[48].

﴿قَالَ رَبِّ إِنِّي ظَلَمۡتُ نَفۡسِي فَٱغۡفِرۡ لِي فَغَفَرَ لَهُۥٓۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ١٦﴾ [القصص: 16]

---

[47] ሱረቱ አሽሹዐራእ፤ ከአንቀፅ 87 - 89

[48] ሱረቱ አንነምል፤ አንቀፅ: 19

37 - {ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ። ለእኔም ማር።}[49].

﴿... رَبِّ نَجِّنِي مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ۝٢١﴾ [القصص: 21]

38 - {ጌታዬ ሆይ! ከበደለኞች ህዝቦች አድነኝ።}[50].

﴿... عَسَىٰ رَبِّيٓ أَن يَهْدِيَنِي سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ۝٢٢﴾ [القصص: 22]

39 - {ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ።}[51].

﴿... رَبِّ إِنِّي لِمَآ أَنزَلْتَ إِلَيَّ مِنْ خَيْرٍ فَقِيرٌ ۝٢٤﴾ [القصص: 24]

40 - {ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደኔ ለምታወርደው ፈላጊ ነኝ።}[52].

﴿قَالَ رَبِّ ٱنصُرْنِي عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْمُفْسِدِينَ ۝٣٠﴾ [العنكبوت: 30]

41 - {ጌታዬ ሆይ! በአመፀኞች ህዝቦች ላይ እርዳኝ።}[53].

---

[49] ሱረቱ አልቀሶስ፤ አንቀፅ: 16

[50] ሱረቱ አልቀሶስ፤ አንቀፅ: 21

[51] ሱረቱ አልቀሶስ፤ አንቀፅ: 22

[52] ሱረቱ አልቀሶስ፤ አንቀፅ: 24

[53] ሱረቱል ዐንከቡት፤ አንቀፅ: 30

﴿رَبِّ هَبۡ لِي مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١٠٠﴾ [الصافات: 100]

42 - {ጌታዬ ሆይ! ከመልካሞቹ የሆነን (ልጅ) ስጠኝ።}[54].

﴿...رَبِّ أَوۡزِعۡنِيٓ أَنۡ أَشۡكُرَ نِعۡمَتَكَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتَ عَلَيَّ وَعَلَىٰ وَٰلِدَيَّ وَأَنۡ أَعۡمَلَ صَٰلِحٗا تَرۡضَىٰهُ وَأَصۡلِحۡ لِي فِي ذُرِّيَّتِيٓۖ إِنِّي تُبۡتُ إِلَيۡكَ وَإِنِّي مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ١٥﴾ [الأحقاف: 15]

43 - {ጌታዬ ሆይ! ያቺን በእኔ ላይና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ጸጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም መልካም ስራ እንድሰራ ምራኝ። ዘሮቼንም ለእኔ አብጅልኝ። እኔ ወዳንተ ተመለስኩ። እኔም ከሙስሊሞች ነኝ።}[55].

﴿... رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا وَلِإِخۡوَٰنِنَا ٱلَّذِينَ سَبَقُونَا بِٱلۡإِيمَٰنِ وَلَا تَجۡعَلۡ فِي قُلُوبِنَا غِلّٗا لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ رَبَّنَآ إِنَّكَ رَءُوفٞ رَّحِيمٌ ١٠﴾ [الحشر: 10]

44 - {ጌታችን ሆይ! ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግ። በልቦቻችንም ውስጥ

---

[54] ሱረቱ አስሷፋት፤ አንቀፅ: 100

[55] ሱረቱ አልአሕቃፍ፤ አንቀጽ: 15

ለእነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ። ጌታችን ሆይ! አንተ ሩህሩህ አዛኝ ነህና።}[56].

﴿... رَّبَّنَا عَلَيۡكَ تَوَكَّلۡنَا وَإِلَيۡكَ أَنَبۡنَا وَإِلَيۡكَ ٱلۡمَصِيرُ ٤﴾ [الممتحنة: 4]

45 - {ጌታችን ሆይ! በአንተ ላይ ተመካን። ወደ አንተም ተመለስን። መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው።}[57].

﴿رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا فِتۡنَةٗ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ وَٱغۡفِرۡ لَنَا رَبَّنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٥﴾ [الممتحنة: 5]

46 - {ጌታችን ሆይ! ለእነዚያ ለካዱት ሰዎች መሞከሪያ አታድርገን። ለእኛም ምህረት አድርግልን። ጌታችን ሆይ! አንተ አሸናፊው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህ።}[58].

﴿... رَبَّنَآ أَتۡمِمۡ لَنَا نُورَنَا وَٱغۡفِرۡ لَنَآۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٨﴾ [التحريم: 8]

[56] ሱረቱ አልሐሽር፤ አንቀፅ: 10

[57] ሱረቱ አልሙምተሒና፤ አንቀፅ: 4

[58] ሱረቱ አልሙምተሒና፤ አንቀፅ: 5

47 - {ጌታችን ሆይ! ብርሀናችንን ሙላልን። ለእኛ ምህረትም አድርግልን። አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና።}[59].

﴿رَّبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَلِوَٰلِدَيَّ وَلِمَن دَخَلَ بَيۡتِيَ مُؤۡمِنٗا وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۖ وَلَا تَزِدِ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا تَبَارَۢا ٢٨﴾ [نوح: 28]

48 - {ጌታዬ ሆይ! ለእኔም ለወላጆቼም ምእመን ሆኖ በቤቴ ለገባም ሰው ሁሉ ለምእመናንና ለምእመናትም ምህረት አድርግ።}[60].

﴿...فَهَدَى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لِمَا ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ مِنَ ٱلۡحَقِّ بِإِذۡنِهِۦۗ وَٱللَّهُ يَهۡدِي مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٍ ٢١٣﴾ [البقرة: 213]

49 - {አላህ ሆይ! ከእውነት በርሱ ለተለያዩበት በፍቃድህ ምራኝ። አንተ የምትሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትመራለህ።}[61]

---

[59] ሱረቱ አትተሕሪም፤ አንቀፅ: 8

[60] ሱረቱ ኑሕ፤ አንቀፅ: 28

[61] ከሱረቱል በቀራህ አንቀፅ፤ 213 የተወሰደ

﴿يُؤۡتِي ٱلۡحِكۡمَةَ مَن يَشَآءُۚ وَمَن يُؤۡتَ ٱلۡحِكۡمَةَ فَقَدۡ أُوتِيَ خَيۡرٗا كَثِيرٗاۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٢٦٩﴾ [البقرة: 269]

50 - {አላህ ሆይ! ጥበብን ስጠኝ። ያ ጥበብን የተሰጠ ሰው በርግጥም ብዙን መልካም ነገር የተሰጠ የሚሆንበት።}[62]

﴿يُثَبِّتُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱلۡقَوۡلِ ٱلثَّابِتِ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِۖ ...٢٧﴾ [إبراهيم: 27]

51 - {አላህ ሆይ! በቅርቢቱም ህይወት ሆነ በመጨረሻው ህይወት በተረጋገጠው ቃል ላይ አፅናኝ።}[63]

﴿... ٱللَّهَ حَبَّبَ إِلَيۡكُمُ ٱلۡإِيمَٰنَ وَزَيَّنَهُۥ فِي قُلُوبِكُمۡ وَكَرَّهَ إِلَيۡكُمُ ٱلۡكُفۡرَ وَٱلۡفُسُوقَ وَٱلۡعِصۡيَانَۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلرَّٰشِدُونَ ٧﴾ [الحجرات: 7]

52 - {አላህ ሆይ! እምነትን ወደእኛ አስወድድ ፣ በልቦቻችን ውስጥም አጊጠው ፣ ወደእኛም ክህደትን፣ አመፅንና እንቢተኝነትን የተጠላ አድርገው። ከቅኖቹም አድርገን።}[64]

---

[62] ከሱረቱል በቀራህ አንቀፅ: 269 የተወሰደ

[63] ከሱረቱል ኢብራሂም አንቀፅ: 27 የተወሰደ

[64] ከሱረቱል ሑጁራት አንቀፅ: 7 የተወሰደ

﴿فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ وَٱسۡمَعُواْ وَأَطِيعُواْ وَأَنفِقُواْ خَيۡرٗا لِّأَنفُسِكُمۡۗ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٦﴾ [التغابن: 16]

53 - {አላህ ሆይ! ከነፍሴ ንፍገት ጠብቀኝ። ስኬትን ከሚጎናፀፉትም አድርገኝ።}[65]

54 -{አላህ ሆይ! በቅርቢቱም ህይወት መልካምን በመጨረሻይቱም ህይወት መልካምን ስጠን። ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን።}[66]

55 -"አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲ-ንናሪ ወዐዛቢ-ንናሪ ወፊትነቲል ቀብሪ ወዐዛቢል ቀብሪ ወሸርሪ ፊትነቲል ኺና ወሸርሪ ፊትነቲል ፈቅሪ ፤ አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ፊትነቲል መሲሒ-ድደጃል ፤ አልላሁምመግሲል ቀልቢ ቢማኢ-ሥሠልጂ ወልበረድ ወነቅቂ ቀልቢ ሚነልኸጧያ ከማ ነቅቀይተ-ሥሠውበል አብየድ ሚነ-ድደነስ ወባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወልመግሪብ ፤ አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነልከሰሊ ወልመእሠሚ

---

65 ከሱረቱ አትተጋቡን አንቀፅ: 16 የተወሰደ

66 ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር 4522 እና 6389 ሲዘግቡት ፤ ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር 2690 ዘግበውታል።

ወልመኛረሚ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከእሳት ፈተና ፣ ከእሳት ቅጣት ፣ ከቀብር ፈተና ፣ ከቀብር ቅጣት ፣ ከሀብት ፈተና ክፋት ፣ ከድህነት ፈተና ክፋት ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! እኔ ከመሲሕ ደጃል ፈተና ክፋት ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ልቤን በጤዛና የበረዶ ውሃ እጠበው ፤ ነጭ ልብስን ከእድፍ እንዳፀዳኸው ልቤንም ከወንጀሎች አፅዳው ፤ በምስራቅና ምዕራብ መካከል እንዳራራቅከው በኔና በወንጀሎቼ መካከልም አራርቅ ፤ አላህ ሆይ! እኔ ከስንፍና ፣ ከወንጀልና ከእዳ ባንተ እጠበቃለሁ።"[67]

56 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነልዐጅዚ ወልከሰሊ ወልጁብኒ ወልሀረሚ ወልቡኽሊ ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢል ቀብሪ ወሚን ፊትነቲል መሕያ ወልመማቲ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከስንፍና ፣ ከመታከት ፣ ከፈሪነት ፣ ከእርጅናና ከስስት ባንተ እጠበቃለሁ። ከቀብር ቅጣት ፣ ከህይወትና ሞት ፈተናም ባንተው እጠበቃለሁ።"[68]

57 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ጀህዲል በላእ ወደረኪ-ሽሽቃእ ወሱኢል ቀዷእ ወሸማተቲል አዕዳእ" ትርጉሙም

---

[67] ቡኻሪይ በቁጥር 832 ፣ ሙስሊም በቁጥር 589 ዘግበውታል።

[68] ቡኻሪይ በቁጥር 2823 ፣ ሙስሊም በቁጥር 2706 ዘግበውታል።

"አላህ ሆይ! እኔ ከከባድ መከራ ፣ እድለ ቢስነት ከሚያገኘኝ ፣ ከመጥፎ ውሳኔ ፣ የጠላት ደስታ ምንጭ ከመሆን ባንተ እጠበቃለሁ።"[69]

58 -"አልሏሁምመ አስሊሕ ሊ ዲኒ-ልለዚ ሁወ ዒስመቱ አምሪ ወአስሊሕ ሊ ዱንያየ-ልለቲ ፊሀ መዓሺ ወአስሊሕ ሊ አኺረቲ-ልለቲ ፊሃ መዓዲ ወጅዐሊል ሐያተ ዚያደተን ሊ ፊ ኩልሊ ኸይር ወጅዐሊል መውተ ራሐተን ሊ ሚን ኩልሊ ሸር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! የጉዳዮቼ መጠበቂያ የሆነውን ሀይማኖቴን አስተካክልልኝ ፤ ኑሮዬ በውስጧ የሆነችውን ዱንያዬንም ለኔ አስተካክልልኝ ፤ መመለሻዬ የሆነችውን አኺራዬንም ለኔ አስተካክልልኝ ፤ ህይወትንም ለኔ መልካም ነገር ሁሉ የምጨምርባት አድርግልኝ ፤ ሞትንም ለኔ ከሁሉም መጥፎ ነገር እረፍት አድርግልኝ።"[70]

---

[69] ቡኻሪይ በቁጥር 6347 ፣ ሙስሊም በቁጥር 2707 የዘገቡት ሲሆን የሙስሊም ዘገባ "የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከከባድ መከራ ፣ በእድለ ቢስነት ከመገኘት ፣ ከመጥፎ ውሳኔ ፣ የጠላት ደስታ ምንጭ ከመሆን ይጠበቁ ነበር።" የሚል ነው።

[70] ሙስሊም በቁጥር 2720 ዘግበውታል።

59 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ሁዳ ወት-ቱቃ ወልዐፋፈ ወልῙና" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ቅናቻን ፣ ጥንቁቅነትን ፣ ጨዋነትንና መብቃቃትን እጠይቅሃለሁ።"[71]

60 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነልዐጅዚ ወልከሰሊ ወልጁብኒ ወልቡኽሊ ወልሀረሚ ወዐዛቢል ቀብር ፤ አልሏሁምመ አቲ ነፍሲ ተቅዋሃ ወዘክኪሃ አንተ ኸይሩ መን ዘክካሃ አንተ ወሊይዩሃ ወመውላሃ ፤ አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዒልሚን ላ የንፈዑ ወሚን ቀልቢን ላ የኽሸዑ ወሚን ነፍሲን ላ ተሽበዑ ወሚን ደዕወቲን ላ ዩስተጃቡ ለሃ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከስንፍና ፣ ከመታከት ፣ ከፈሪነት ፣ ከስስት ፣ ከመጃጀትና ከቀብር ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ለነፍሴ ፍራቻዋን ስጣት ፤ ነፍሴን ለማጥራት የተሻልከው አንተው ነህና ነፍሴን አጥራት ፤ አንተ ረዳቷና ተቆጣጣሪዋ ነህና። አላህ ሆይ! እኔ ከማይጠቅም እውቀት፣ ከማይተናነስ ልብ፣ ከማትጠግብ ነፍስ፣ ተቀባይነት ከሌላት ዱዓም ባንተ እጠበቃለሁ።"[72]

---

[71] ሙስሊም በቁጥር 2721 ዘግበውታል።

[72] ሙስሊም በቁጥር 2722 ዘግበውታል።

61 -"አልሏሁምመህዲኒ ወሰድዲድኒ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ሁዳ ወስሰዳድ" "አላህ ሆይ! ምራኝ ግጠመኝም። አላህ ሆይ! እኔ ቅናቻንና መገጠምን እጠይቅሃለሁ።"[73]

62 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዘዋሊ ኒዕመቲከ ወተሐውዉሊ ዓፊየቲከ ወፉጃአቲ ኒቅመቲከ ወጀሚዒ ሰኸጢክ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከፀጋህ መወገድ ፣ (ከሰጠኸኝ) ጤንነት መቀልበስ ፣ ከድንገተኛ ቅጣትህና ከአጠቃላዩ ቁጣህ ባንተው እጠበቃለሁ።"[74]

63 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማ ዐሚልቱ ወሚን ሸርሪ ማ ለም አዕመል" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከሰራሁትም ክፋት ካልሰራሁትም ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ።"[75]

64 -"አልሏሁምመ አክሢር ማሊ ወወለዲ ወባሪክ ሊ ፊማ አዕጦይተኒ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ገንዘቤን፣ ልጄን፣ አብዛልኝ ፤ በሰጠኸኝም ነገር ላይ በረካ አድርግልኝ።"[76]"(ወአጢል ሐያቲ

---

[73] ሙስሊም በቁጥር 2725 ዘግበውታል።

[74] ሙስሊም በቁጥር 2739 ዘግበውታል።

[75] ሙስሊም በቁጥር 2716 ዘግበውታል።

[76] ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለአነስ "አላህ ሆይ! ገንዘቡንና ልጁን አብዛለት ፣ ለሱ በሰጠኸውም ነገር ባርክለት።" በማለት ያደረጉለት ዱዓ

ዓላ ጧዐቲከ ወአሕሲን ዐመሊ) ወሻፊር ሊ" ትርጉሙም "(ህይወቴንም አንተን በማምለክ ላይ አርዝምልኝ ፣ ስራዬን አሳምርልኝ) ፣ ለኔ ማረኝም።"77

65 -"ላ ኢላሃ ኢልለሏሁል ዐዚሙል ሐሊም ፤ ላ ኢላሃ ኢልለሏሁ ረብቡል ዐርሺል ዐዚም ፤ ላ ኢላሃ ኢልለሏሁ ረቡስሰማዋቲ ወረቡል አርዲ ወረቡል ዐርሺል ከሪም" ትርጉሙም " ከታላቁና ቻይ ከሆነው አላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። የታላቁ ዐርሽ ጌታ ከሆነው አላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። የሰማያት ጌታ ፣ የምድር

---

ይህንኑ ያመላክታል። በቁጥር 1982 ቡኻሪ በቁጥር 660 ሙስሊም ዘግበውታል።

[77] ቡኻሪ በአደቡል ሙፍረድ በቁጥር 653 ሲዘግቡት አልባኒይም በሲልሰለቱል አሓዲሠ ሶሒሓ በቁጥር 2241 ላይና በሶሒሕ አልአደቡል ሙፍረድ ገፅ 244 ውስጥ ሶሒሕ ብለውታል። በቅንፉ ውስጥ የተጠቀሰው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም “ከሰዎች ሁሉ ምርጡ ማነው?” ተብለው በተጠየቁ ጊዜ "እድሜው ረዝሞ ስራው ያማረ።" በማለት የመለሱበት ሐዲስ የሚጠቁመን ነው። ቲርሚዚይ በቁጥር 2329 ፣ አሕመድ በቁጥር 17716 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በሶሒሕ አትቲርሚዚ 2/271 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። ታላቁ ሸይኻችን ኢብኑ ባዝን (አላህ ይዘንላቸውና) “ይህንን ዱዓ ማድረግ ሱና ነውን?” ብዬ ጠይቄያቸው እሳቸውም "አዎ" ብለውኛል።

ጌታ ፣ የተከበረው ዐርሽ ጌታ ከሆነው አላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም።"[78]

66 -"አልሏሁምመ ራሕመተከ አርጁ ፈላ ተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጦርፈተ ዐይኒን ወአስሊሕ ሊ ሻእኒ ኩልለሁ ላ ኢላሃ ኢልላ አንተ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እዝነትህን እከጅላለሁና የአይን መርገብገብን ያህል እንኳ ቢሆን ለራሴ አትተወኝ ፤ ጉዳዬንም ሁሉ አስተካክልልኝ። ከአንተ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም።"[79]

67 -"ላ ኢላሃ ኢለላ አንተ ሱብሓነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚነዝዟሊሚን" ትርጉሙም "ከአንተ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ጥራት ይገባህ! እኔ ከበዳዮች ነበርኩ። "[80]

---

[78] ቡኻሪ በቁጥር 6345፤ ሙስሊም በቁጥር 2730 ላይ ዘግበውታል።

[79] ኡቡዳውድ በቁጥር 5090 ፣ አሕመድ በ5/42 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በሶሒሕ አቡዳውድ 3/250 እና በሶሒሕ አልአደቡል ሙፍረድ 260 ላይ ሐሰን ብለውታል። በተጨማሪ ታላቁ ሊቅ ኢብኑ ባዝም በቱሕፈቱል አኽያር ገፅ 24 ላይ ሰነዱን ሐሰን ብለውታል።

[80] ቲርሚዚይ በቁጥር 3505 ላይ ዘግበውታል። ሐኪምም ዘግበውት ሶሒሕ ብለውታል። ዘሀቢም በ1/505 ሶሒሕ በሚለው ላይ ከሐኪም ጋር ገጥመዋል። አልባኒም በሶሒሕ ቲርሚዚ 3/168 ውስጥ ሶሒሕ ብለውታል።

68 -"አልኋሁምመ ኢንኒ ዐብዱከ ኢብኑ ዐብዲከ ኢብኑ አመቲከ ናሲየቲ ቢየዲከ ማዷን ፊይየ ሑክሙከ ዐድሉን ፊይየ ቀዷኡከ አስአሉከ ቢኩልሊ ኢስሚን ሁወ ለከ ሰመይተ ቢሂ ነፍሰከ አው አንዘልተሁ ፊ ኪታቢከ አው ዐለምተሁ አሐደን ሚን ኸልቂከ አው ኢስተእሠርተ ቢሂ ፊ ዒልሚል ቫይቢ ዒንደከ አንተጅዐለል ቁርአነ ረቢዐ ቀልቢ ወኑረ ሶድሪ ወጀላአ ሑዝኒ ወዘሃበ ሀምሚ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ባሪያህ ነኝ። የወንድ ባሪያህና የሴት ባሪያህ ልጅ ነኝ። አናቴ በእጅህ ነው ፣ ፍርድህ በኔ ላይ ተፈፃሚ ነው ፣ በኔ ላይ የምትወስነው ውሳኔህ ፍትሃዊ ነው። ነፍስህን በሰየምክበት ስሞችህ፣ ወይም በመፅሀፍህ ውስጥ ባወረድከው ስሞችህ፣ ወይም ከፍጥረታትህ አንዱን ባሳወቅከውም ስሞችህ፣ ወይም አንተ ዘንድ በሩቅ እውቀትህ በተለየህበት ስሞችህ፣ በሁሉም ላንተ ባሉህ ስሞች ቁርአንን

---

የሐዲሱ ቃልም "ዘኑን ዓሳነባሪ ሆድ ውስጥ ሆኖ የተጣራውን ጥሪ (አን ላ ኢላሃ ኢልላ አንተ ሱብሓነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚነዝዟሊሚን) (ትርጉሙም: ካንተ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ጥራት ይገባህ! እኔ ከበዳዮች ነበርኩ።) አንድ ሙስሊም የሆነ ሰው በአንዳች ጉዳዩ ላይ በዚህ ጥሪ በጭራሽ (አኋህን) አይጣራም (አይማጸንም) አላህ ለርሱ የሚቀበለው ቢሆን እንጂ።"

የልቤ ፀደይ፣ የልቤ ብርሀን፣ የሀዘኔ ማንሻ፣ የጭንከቴ ማስወገጃ እንድታደርግልኝ እጠይቅሃለሁ።"[81]

69 -"አልሏሁምመ ሙሶርሪፈል ቁሉቢ ሶሪፍ ቁሉበና ዓላ ጧዐቲክ" ትርጉሙም "ልቦናን አዟሪ የሆንከው አላህ ሆይ! ልቦናችንን ወደ አምልኮህ አዙር!"[82]

70 -"ያ ሙቀልሊበል ቁሉቢ ሠብቢት ቀልቢ ዓላ ዲኒክ" ትርጉሙም "ልቦናን ገለባባጭ የሆንከው ሆይ! ልቤን በአንተ ሃይማኖት ላይ አፅናት! "[83]

---

[81] አሕመድ በ 1/391 ና 452 ላይ ፣ ሓኪም በ1/509 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልሐፊዝ "አልአዝካር"ን ተኽሪጅ ባደረጉበት ውስጥ ሐሰን ብለውታል። አልባኒም "አልከሊሙ ጠዪብ"ን ተኽሪጅ ባደረጉበት ኪታብ 73ኛ ገፅ ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[82] ሙስሊም በቁጥር 2654 ላይ ዘግበውታል።

[83] ቲርሚዚ በቁጥር 3522 ፣ አሕመድ በ4/182 ላይ ዘግበውታል፤ ሓኪምም በ1/525 ዘግበው ሶሒሕ ያሉት ሲሆን ዘሀቢም ገጥመዋቸዋል። አልባኒም በሶሒሕ አልጃሚዕ በ6/309 ላይና በሶሒሕ ቲርሚዚ 3/171 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። ኡሙ ሰለማ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- "የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የአብዛኛው ጊዜ ዱዓቸው ይህ ነበር።" ብላለች።

71 -"አልኋሁምመ ኢንኒ አስአሉከል የቂነ ወልዐፍወ ወልዓፊየተ ፊድዱንያ ወልአኺራህ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ በዱንያ ውስጥም ሆነ በአኺራ እርግጠኛ እምነትን፣ ይቅርታህንና ጤናን እጠይቅሃለሁ።"[84]

72 -"አልኋሁምመ አሕሲን ዓቂበተና ፊል ኡሙሪ ኩልሊሃ ወአጂርና ሚን ኺዝዪ-ድዱንያ ወዐዛቢል አኺረህ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በሁሉም ጉዳዮች ፍፃሜያችንን አሳምርልን ፤ ከዱንያ ውርደትና ከአኺራ ቅጣትም ጠብቀን።"[85]

---

[84] ቲርሚዚይ ቁጥር 3514 ፣ ቡኻሪይም በአደቡል ሙፍረድ ውስጥ ቁጥር 726 ላይ ዘግበውታል። የቲርሚዚ ዘገባ ውስጥ ያለው ቃል "አላህን በዱንያም ሆነ በአኺራ (ዓፊያን) ጤናማነትን ጠይቁት" በሌላ ዘገባ "አላህን ይቅርታውንና ጤናማነትን ጠይቁት! አንዳችሁም ከእርግጠኛ እምነት በኋላ ከጤናማነት የተሻለ ነገር አያገኝምና።" የሚል ነው። አልባኒ በሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ 3/180፣ 3/185፣ 3/170 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። ይህን ሐዲሥ የሚያመሰክሩ ሌሎች ሐዲሶችም አሉ። አሕመድ ሻኪር ባጠናቀሩት ሙስነድ ኢማሙ አሕመድ ውስጥ 1/156 - 157 ላይ ይመልከቱ።

[85] አሕመድ በ4/181 ፣ ጦበራኒ በ "አልከቢር" 2/33 እና 1169 ላይ ፣ "አድዱዓእ" በሚለው መፅሀፍም በቁጥር 1436 ፣ ኢብኑ ሒባን በቁጥር 2424 እና 2425 ላይ ዘግበውታል። አልሐፊዝ ሀይሠሚይ በመጅመዑ-ዝዘዋኢድ 10/178 ላይ "አሕመድ የዘገቡት ላይ ያሉ ዘጋቢዎችና የጦበራኒ አንዱ ሰነድ ላይ ያሉ ዘጋቢዎች ታማኝ ናቸው።" ብለዋል።

73 -"ረብቢ አዒንኒ ወላ ቱዒን ዐለይየ ወንሱርኒ ወላ ተንሱር ዐለይየ ወምኩር ሊ ወላ ተምኩር ዐለይየ ወህዲኒ ወየስሲረል ሁዳ ኢለይየ ወንሱርኒ ዓላ መን በቻ ዐለይየ ረብቢጅዐልኒ ለከ ሸክካረን ለከ ዘክካረን ለከ ረህሃበን ለከ ሚጥዋዓን ኢለይከ ሙኽቢተን አውዋሃን ሙኒበን ረብቢ ተቀብበል ተውበቲ ወቫሲል ሐውበቲ ወአጂብ ደዕወቲ ወሠብቢት ሑጅጀቲ ወህዲ ቀልቢ ወሰድዲድ ሊሳኒ ወስሉል ሰኺመተ ቀልቢ" ትርጉሙም "ጌታዬ አግዘኝ እኔን በመጉዳት ላይ ማንንም አታግዝ ፣ እርዳኝ እኔን በመጉዳት ላይ ማንንም አትርዳ ፣ (ጠላቶቼን) ሳያስቡት ለኔው ያዝልኝ እንጂ እኔን ሳላስበው አትያዘኝ ፣ ምራኝ መመራትንም ለኔ አግራልኝ ፣ በኔ ላይ ወሰን ባለፈ ላይ እርዳኝ ፣ ጌታዬ ላንተ እጅግ አመስጋኝህ ፣ እጅግ የሚያወሳህ ፣ እጅግ ፈሪህ ፣ እጅግ ታዛዥህ ፣ ወዳንተ ተናናሽ ፣ በፀፀት ተመላሽ አድርገኝ ፤ ጌታዬ ተውበቴንም ተቀበል ፤ ወንጀሌን እጠብ ፣ ልመናዬን ተቀበል ፣ ማስረጃዬን አፅና ፣ ቀልቤን ምራ ፣ ምላሴን (እውነት እንድታወራ) ቀጥ አድርጋት ፣ የልቤን ምቀኝነት አውጣልኝ።"[86]

---

[86] ቡኻሪ በ "አደቡል ሙፍረድ" ቁጥር 664 እና 665 ላይ ፣ አቡዳውድ በቁጥር 1510 እና 1511 ላይ ፣ ቲርሚዚ በቁጥር 3551 ፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3830 ፣ አሕመድ በ1/127 የዘገቡት ሲሆን ሐኪም ሶሒሕ ብለውት ዘሀቢም በ1/519 ከሐኪም ጋር ተስማምተዋል። አልባኒም በሶሒሕ አቡዳውድ 1/414 እና በሶሒሕ ቲርሚዚ 3/178 ውስጥ ሶሒሕ ብለውታል።

74 -"አልኋሁምመ ኢንና ነስአሉከ ሚን ኸይሪ ማ ሰአለከ ሚንሁ ነቢይዩከ ሙሐመዱን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ወነዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ መስተዓዘ ሚንሁ ነቢይዩከ ሙሐመዱን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ወአንተል ሙስተዓኑ ወዐለይከል በላኙ ወላ ሓውለ ወላ ቁወተ ኢልላ ቢልላህ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኛ ነብይክ ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የጠየቁህን መልካም ነገር እንጠይቅሃለን። ነብይክ ሙሐመድ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከተጠበቁበት መጥፎ ነገርም ባንተው እንጠበቃለን። አንተ እገዛ የሚፈለግብህ ነህ። ባንተ እገዛ ነው (ወደ አላማ) የሚደረሰው። በአላህ ካልሆነ በቀር መለወጥም ሀይልም የለም።"[87]

75 -"አልኋሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ሰምዒ ወሚን ሸርሪ በሶሪ ወሚን ሸርሪ ሊሳኒ ወሚን ሸርሪ ቀልቢ ወሚን ሸርሪ መኒይዪ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከመስሚያዬ ክፋት ፣

[87] ቲርሚዚ በቁጥር 3521 ፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3846 ተመሳሳይ ሀሳብ ያለውን ዘግበዋል። ቲርሚዚ "ይህ ሐዲስ ሐሰኑን ኻሪብ ነው።" ብለዋልም። አልባኒ በ "ዶዒፍ አትቲርሚዚ" ገፅ 387 ላይ ዶዒፍ ብለውታል።

ከአይኔ ክፋት ፣ ከምላሴ ክፋት ፣ ከልቤ ክፋት ፣ ከዘር ፈሳሼ ክፋት ባንተ እጠበቃለሁ።"[88]

76 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል በረሲ ወልጁኑኒ ወልጁዛሚ ወሚን ሰይዪኢል አስቃሚ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከለምጥ ፣ ከእብደት፣ ከቁምጥና፣ ከመጥፎ በሽታዎችም ባንተ እጠበቃለሁ።"[89]

77 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሙንከራቲል አኽላቂ፣ ወልአዕማሊ፣ ወልአህዋእ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከመጥፎ ስነ ምግባሮች ፣ ተግባሮችና ዝንባሌዎች ባንተ እጠበቃለሁ።"[90]

---

[88] አቡዳውድ ቁጥር 1551 ፣ ቲርሚዚ ቁጥር 3492 ፣ ነሳኢ ቁጥር 5470 ላይ እና ሌሎችም የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" 3/166 እና በ "ሶሒሕ አንነሳኢ" 3/1108 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[89] አቡዳውድ ቁጥር 1554 ላይ ፣ ነሳኢ ቁጥር 5493 ላይ ፣ አሕመድ 3/192 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ አንነሳኢ" ቁጥር 3/1116 ላይ እና በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" ቁጥር 3/184 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[90] ቲርሚዚ ቁጥር 3591 ፣ ኢብኑ ሒባን ቁጥር 2422፣ ሐኪም 1/532 ላይ ፣ ጦበራኒ "አልከቢር" ውስጥ 19/36 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" 3/184 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

78 -"አልሏሁምመ ኢንነከ ዐፉውዉን ከሪሙን ቱሒብቡል ዐፍው ፈዕፉ ዐንኒ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! አንተ ይቅር ባይ ፣ ቸር ነህ። ይቅር ባይነትንም ትወዳለህና ለኔ ይቅር በለኝ።"[91]

79 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ፊዕለል ኸይራቲ ፣ ወተርከል ሙንከራቲ ፣ ወሑብበል መሳኪኒ ፣ ወአንተግፊረ ሊ ወተርሐምኒ ። ወኢዛ አረድተ ፊትነተ ቀውሚን ፈተወፍፈኒ ኻይረ መፍቱኒን። ወአስአሉከ ሑብበከ፣ ወሑብበ መን ዩሒብቡከ፣ ወሑብበ ዐመሊን ዩቀርሪቡኒ ኢላ ሑብቢክ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ መልካም መስራትን፣ መጥፎ መተውን፣ ሚስኪኖች መውደድን፣ ለኔ እንድትምረኝ፣ እንድታዝንልኝም እጠይቅሃለሁ። ህዝቦችን መፈተን የፈለግክ ጊዜ እኔን ሳትፈትን ግደለኝ። ውዴታህን ፣ የሚወዱህን መውደድ ፣ ወደ ውዴታህ የሚያቃርበኝን ስራ መውደድን (እንድትሰጠኝ) እጠይቅሃለሁ።[92]

---

[91] ቲርሚዚ ቁጥር 3513 ፣ ነሳኢ በ "አልኩብራ" ውስጥ ቁጥር 7712 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" 3/170 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[92] አሕመድ በዚሁ ቃል በ5/243 ውስጥ ፣ ቲርሚዚ ቁጥር 3235 ላይ በተመሳሳይ ዘግበውት ሐሰን ብለውታል። ቲርሚዚ እንዲህ ብለዋል "ሙሐመድ ቢን ኢስማዒልን (ቡኻሪን) ስለዚህ ሐዲስ ደረጃ ጠየቅኩት። ቡኻሪም 'ይህ ሐዲስ ሐሰኑን ሶሒሕ ነው።' ብሎኛል።" በሐዲሱ መጨረሻ

80 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚነል ኸይሪ ኩልሊሂ ዓጂሊሂ ወኣጂሊሂ፣ ማ ዐሊምቱ ሚንሁ ወማ ለም አዕለም ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነሸሪ ኩሊሂ ዓጂሊሂ ወኣጂሊሂ፣ ማ ዐሊምቱ ሚንሁ ወማ ለም አዕለም ፤ አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ኸይሪ ማ ሰአለከ ዐብዱከ ወነቢይዩክ ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ መስተዓዘ ቢከ ሚንሁ ዐብዱከ ወነቢይዩክ ፤ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከል ጀንነተ ወማ ቀርረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመል ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነንናሪ ወማ ቀርረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመል፤ ወአስአሉከ አንተጅዐለ ኩለ ቀዷኢን ቀዶይተሁ ሊ ኸይራ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከሁሉም መልካም ነገር እጠይቅሀለሁ ፤ ከፈጣኑም ይሁን ከዘገየው፣ ካወቅኩትም ይሁን ካላወቅኩት። ከሁሉም መጥፎ ነገርም ባንተ እጠበቃለሁ፤ ከፈጣኑም ይሁን ከዘገየው፣ ካወቅኩትም ይሁን ካላወቅኩት። አላህ ሆይ! እኔ ባሪያህና ነቢይህ የጠየቁህን መልካም ነገር እጠይቅሀለሁ። ባሪያህና ነቢይህ ባንተ የተጠበቁበትን መጥፎ ነገርንም ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! እኔ ጀነትንና ወደርሷ የሚያቃርበን ንግግር ወይም ተግባር

---

ላይ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ "ይህቺ ልትማሯትና ልትቀስሟት የተገባች ዱዓ ናት።" ሐኪምም 1/521 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" 3/318 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

እጠይቅሀለሁ። ከእሳትና ወደርሷ ከሚያቃርብ ንግግር ወይም ተግባር ባንተ እጠበቃለሁ። ሁሉንም ለኔ የወሰንከውን ውሳኔ መልካም እንድታደርግ እጠይቅሀለሁ።"[93]

81 -"አልሏሁምመ ኢሕፈዝኒ ቢልኢስላሚ ቃኢመን፤ ወሕፈዝኒ ቢልኢስላሚ ቃዒደን፤ ወሕፈዝኒ ቢልኢስላሚ ራቂደን፤ ወላ ቱሽሚት ቢየ ዐዱውወን ወላ ሐሲደን፤ አልሏሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚን ኩልሊ ኸይሪን ኸዛኢኑሁ ቢየዲክ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ኩልሊ ሸርሪን ኸዛኢኑሁ ቢየዲክ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ቆሜም በእስልምና ላይ ጠብቀኝ ፤ ተቀምጬም በእስልምና ላይ ጠብቀኝ ፤ ተኝቼም በእስልምና ላይ ጠብቀኝ ፤ ጠላትንና ምቀኛን በኔ አታስደስታቸው ፤ አላህ ሆይ! የሁሉም መልካም ነገር ካዝና በእጅህ ነውና ከሁሉም መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ ፤ የሁሉም መጥፎ ነገር

---

[93] ኢብኑ ማጀህ በዚሁ ቃል ቁጥር 3846 ላይ አሕመድም 6/134 ላይ ዘግበውታል፤ ሁለተኛው ጭማሪ የአሕመድ ዘገባ ነው፤ ሐኪም ሶሒሕ ብለውት፤ ዘሀቢም በ1/521 ከሐኪም ጋር ተስማምተዋል፤ የመጀመሪያው ጭማሪ የዘሃቢ ዘገባ ነው፤ አልባኒም በ "ሶሒሕ ኢብኑ ማጃህ" 2/327 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

(መጠበቂያ) ካዝናው በእጅህ ነውና ከሁሉም መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ።"[94]

82 -"አልሏሁምመ ኢቅሲም ለና ሚን ኸሽየቲከ ማ ተሑሉ ቢሂ በይነና ወበይነ መዓሲከ፤ ወሚን ጧዐቲከ ማ ቱበልሊኙና ቢሂ ጀንነተክ፤ ወሚነል የቂኒ ማ ቱሀውዊኑ ቢሂ ዐለይና መሷኢበ-ድዱንያ፤ አልሏሁምመ መትቲዕና ቢአስማዒና፣ ወአብሷሪና፣ ወቁውዋቲና ማ አሕየይተና፤ ወጅዐልሁል ዋሪሠ ሚንና፤ ወጅዐል ሠእረና ዓላ መን ዘለመና፤ ወንሱርና ዓላ መን ዓዳና፤ ወላተጅዐል ሙሲበተና ፊ ዲኒና፤ ወላተጅዐሊድ-ዱንያ አክበረ ሀምሚና ወላመብለኻ ዒልሚና፤ ወላ ቱሰሊጥ ዐለይና መንላ የርሐሙና" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በኛና አንተን በመወንጀል መካከል የምትጋርድ ከሆነችው ፍራቻህ ለኛ ክፈልልን ፤ ጀነትህ የምታደርሰን ከሆነችው አምልኮህም ለኛ ክፈልልን ፤ የዱንያን መከራ በኛ ላይ የምታቀልልን ከሆነችው እርግጠኛ እምነትም ለኛ ክፈልልን ፤ አላህ ሆይ! በህይወት እስካኖርከን ድረስ በመስሚያችን፣ በአይናችን፣ በሀይላችን አጣቅመን ፤ (እነዚህ አካላቶቻችንንም) እኛን ወራሽ

---

[94] ሐኪም 1/525 ላይ ዘግበውት ሶሒሕ ብለውት ዘሀቢም ተስማምተዋል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" 2/398 እና በ "ሲልሲለቱል አሓዲሣ አስሶሒሐህ" 4/54 ቁጥር 1540 ላይ ሐሰን ብለውታል።

አድርጋቸው ፤ በቀላችንንም በበደሉን ሰዎች ላይ አድርግልን ፤ ጠላት ባደረገን ላይም እርዳን ፤ መከራችንን በሃይማኖታችን ላይ አታድርግ ፤ ዱንያንም ትልቁ ጭንቀታችንና የእውቀታችን መጨረሻ አታድርግብን ፤ የማያዝንልንንም በኛ ላይ አትሹምብን።"[95]

83 -"አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ጁብኒ ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ቡኽሊ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን አን ኡረድደ ኢላ አርዘሊል ዑሙር፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲድ-ዱንያ ወዐዛቢል ቀብር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከፈሪነት ባንተ እጠበቃለሁ ፣ ከስስታምነትም ባንተ እጠበቃለሁ ፣ ወደ ወራዳው እድሜ ከመመለስም ባንተ እጠበቃለሁ ፣ ከዱንያ ፈተናና ከቀብር ቅጣትም ባንተ እጠበቃለሁ ።"[96]

84 -"አልሏሁምመ ኢግፊር ሊ ኸጢአቲ፣ ወጀህሊ፣ ወኢስራፊ ፊ አምሪ፣ ወማ አንተ አዕለሙ ቢሂ ሚንኒ፤

---

[95] አትቲርሚዚ በቁጥር 3502 ፣ ሐኪም በ1/528 ዘግበው ሶሒሕ ሲሉት ዘሀቢም ተስማምተውበታል ፣ ኢብኑ ሱኒ በቁጥር 446 ዘግበውታል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አትቲርሚዚ" 3/168 እና በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" 1/400 ሐሰን ብለውታል።

[96] ቡኻሪ ቁጥር 2822 ላይ ዘግበውታል።

አልሏሁምመ ኢቫፊር ሊ ሀዝሊ፣ ወጇድዲ፣ ወኸጦኢ፣ ወዐምዲ። ወኩልሉ ዛሊከ ዒንዲ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ወንጀሌን፣ አለማወቄን፣ በጉዳዬ ማባከኔን፣ አንተ በኔ ጉዳይ ያወቅከውንም ወንጀል ለኔ ማረኝ፤ አላህ ሆይ! ቀልዴንም፣ ምሬንም፣ ስህተቴንም፣ ሆን ብዬ የሰራሁትንም ለኔ ማረኝ! ይህ ሁሉ ከኔው (ስህተት) ናቸውና።"[97]

85 -"አልሏሁምመ ኢንኒ ዞለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሢራ። ወላ የቫፊሩዝ-ዙኑበ ኢላ አንተ ፈቫፊር ሊ መቫፊረተን ሚን ዒንዲከ ወርሐምኒ ኢንነከ አንተል ቫፉሩር-ረሒም" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ነፍሴን ብዙ በደል በድያታለሁ። ወንጀሎችን ካንተ በቀር ማንም አይምርምና ካንተ ዘንድ በሆነች ምህረት ለኔ ማረኝም እዘንልኝም። እነሆ አንተ እጅግ መሀሪውና አዛኙ ነህና።"[98]

86 -"አልሏሁምመ ለከ አስለምቱ፣ ወቢከ አመንቱ፣ ወዐለይከ ተወከልቱ፣ ወኢለይከ አነብቱ፣ ወቢከ ኻሰምቱ።

---

[97] ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተውበታል። ቡኻሪ ቁጥር 6398 ላይ እና ሙስሊም ቁጥር 2719 ላይ ዘግበውታል።

[98] ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተው ዘግበውታል። ቡኻሪ ቁጥር 834 ላይ እና ሙስሊም ቁጥር 2705 ላይ ዘግበውታል።

አልሏሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢዒዝዘቲከ ላኢላሃ ኢልላ አንተ አን ቱዷለኒ አንተል ሐይዩ ለዚ ላየሙቱ ወልጂንኑ ወልኢንሱ የሙቱን" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ላንተ ትእዛዝ እጅ ሰጠሁ፣ ባንተም አመንኩ፣ ባንተም ላይ ተመካሁ፣ ወዳንተም ተመለስኩ፣ ባንተ መንገድ ላይም ተሟገትኩ። አላህ ሆይ! እኔ እንዳታጠመኝ በልቅናህ እጠበቃለሁ። ከአንተ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም። አንተ የማይሞት ህያው ነህ። ሰውና ጋኔን ይሞታሉ።"[99]

87 -"አልሏሁምመ ኢንና ነስአሉከ ሙጂባቲ ረሕመቲከ፣ ወዐዛኢመ መቫፊረቲከ፣ ወስሰላመተ ሚን ኩሊ ኢሥም፣ ወልቫኒመተ ሚን ኩልሊ ቢር፣ ወልፈውዘ ቢልጀንነቲ፣ ወንነጃተ ሚነ-ንናር" "አላህ ሆይ! እኛ እዝነትህን የሚያስገድዱ ነገሮችን፣ ምህረትህን የሚያስፈርዱ ነገሮችን፣ ከሁሉም ወንጀል ሰላም መሆንን፣ ከሁሉም መልካም ስራ መሸመትን፣ በጀነት ስኬት መጎናፀፍንና ከእሳት መዳንን እንጠይቅሀለን።"[100]

---

[99] ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተውበታል። ቡኻሪ ቁጥር 6398 ላይ እና ሙስሊም ቁጥር 2719 ላይ ዘግበውታል።

[100] ሐኪም በ1/525 ዘግበው ሶሒሕ ያሉት ሲሆን ዘሀቢም ተስማምተውበታል ፣ በይሀቂ "አድደዓዋት" ውስጥ ቁጥር 206 ላይ

88 -"አላሁመሻፊር ሊልሙእሚኒነ ወልሙእሚናት" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ለአማኝ ወንዶችና ሴቶች ማር።"[101]

89 -"አላሁመሻፊርሊ ዘንቢ፣ ወወሲዕ ሊ ፊ ዳሪ፣ ወባሪክ ሊ ፊ ማ ረዘቅተኒ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ፣ መኖሪያ ሀገሬንም አስፋልኝ፣ በሰጠኸኝም ሲሳይ ባርክልኝ።"[102]

---

ዘግበውታል። የነወዊን "አልአዝካር" ገፅ 340 ላይ ይመልከቱ። አርታዒው ዐብዱል ቃድር አልአርነኡጥ ሓሰን ብለውታል።

[101] በዑባዳ ሀዲስ -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ አለ: "ለአማኝ ወንዶችና ሴቶች ምህረትን የጠየቀላቸው አላህ በሁሉም አማኝ ወንድና ሴት ልክ ምንዳን ይፅፍለታል።" ይህንንም ሀዲስ ጦበራኒ "አልከቢር" ውስጥ በ5/202 ቁጥር 5092 ላይና በ3/334 ቁጥር 2155 ላይ የዘገቡት ሲሆን ሀይሠሚ በ "መጅመዕ አዝዘዋኢድ" 10/210 ውስጥ ሰነዱን ጠንካራ አድርገውታል። አልባኒም በ "ሶሒሑል ጃሚዕ" በ5/242 ቁጥር 5902 ላይ ሐሰን ብለውታል።

[102] አሕመድ በ4/63 ቁጥር 16599፣ ቁጥር 23114፣ ቁጥር 23188 ላይ፤ ቲርሚዚይ ቁጥር 3500 ላይ ዘግበውታል። የሙስነዱ አርታኢ በ27/144፣ በ38/197 ፣ በ38/197፣ በ38/145 ሐሰን ሊኻይሪሂ ነው ብለዋል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" 1/399 ላይ ሐሰን ብለውታል።

90 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊከ ወረሕመቲከ ፈኢነሁ ላ የምሊኩሀ ኢላ አንተ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከችሮታህና ከእዝነትህ እጠይቅሀለሁ። እነሆ ካንተ በስተቀር ሌላ ባለቤት የላትምና።"[103]

91 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሀረሚ፣ ወትተረዲ፣ ወልሀድሚ፣ ወልቫሚ፣ ወልቫረቂ፣ ወልሐረቅ፤ ወአዑዙ ቢከ አንየተኸበጦኒየሽ-ሸይጧኑ ዒንደል መውት፤ ወአዑዙ ቢከ አን አሙተ ፊ ሰቢሊከ ሙድቢረን፤ ወአዑዙ ቢከ አንአሙተ ለዲቛ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከመጃጀት፣ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ከመውደቅ፣ በኔ ላይ ከሚደረመስብኝ፣ ከጭንቀት፣ ከመስመጥ፣ ከመቃጠል ባንተ እጠበቃለሁ። የሞት ወቅት ላይ የሰይጣን መጫወቻ ከመሆንም ባንተ እጠበቃለሁ።

---

[103] ጦበራኒ የዘገቡት ሲሆን ሀይሠሚ በ "መጅሙዑዝ-ዘዋኢድ" ውስጥ 10/159 ላይ (ከሙሐመድ ቢን ዚያድ ውጪ ሰነዱ ላይ ያሉት ሰዎች የሶሒሕ ዘጋቢዎች ሰዎች ናቸው። እሱም ቢሆን ታማኝ ነው።" ብሏል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" 1/404 ቁጥር 1278 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ከመንገድህ የዞረ ሆኖ ከመሞት ባንተ እጠበቃለሁ። ተነድፎ ከመሞትም ባንተ እጠበቃለሁ።"[104]

92 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልጁዒ ፈኢነሁ ቢእሰድ-ዶጂዑ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ኺያነቲ ፈኢነሀ ቢእሰቲል ቢጧነህ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ረሀብ መጥፎው የመኝታ ባልደረባ ነውና እኔ ከረሀብ ባንተ እጠበቃለሁ፤ ከዳተኝነት መጥፎዋ የውስጥ ልብስ ናትና ከከዳተኝነትም ባንተ እጠበቃለሁ።"[105]

93 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ዐጅዚ፣ ወልከሰሊ፣ ወልጁብኒ፣ ወልቡኽሊ፣ ወልሀረሚ፣ ወልቀስወቲ፣ ወልኀፍለቲ፣ ወልዐይለቲ፣ ወዝዘለቲ፣ ወልመስከነህ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ፈቅሪ፣ ወልኩፍሪ፣ ወልፉሱቂ፣ ወሽሺቃቂ፣ ወንኒፋቂ፣ ወስሱምዐቲ፣ ወርሪያእ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነስሶመሚ፣ ወልበከሚ፣ ወልጁኑኒ፣ ወልጁዛሚ፣ ወልበረሲ፣ ወሰዪኢል አስቃም" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ካለመቻል፣ ከስንፍና፣

---

[104] አቡዳውድ በቁጥር 1552 ፣ ነሳኢ በቁጥር 5531 እና 5532 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ አንነሳኢ" 3/1123 እና በ "ሶሒሕ ሱነን አቡዳውድ" 1/425 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[105] አቡዳውድ በቁጥር 1547፣ ነሳኢ በቁጥር 5483 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ ነሳኢ" 3/1112 ውስጥ ሐሰን ብለውታል።

ከፈሪነት፣ ከስስታምነት፣ ከመጃጀት፣ ከቀልብ ድርቅና፣ ከዝንጉነት፣ ከድህነት፣ ከወራዳነት፣ ከሚስኪንነት ባንተ እጠበቃለሁ። ከድህነት፣ ከክህደት፣ ከአመፀኝነት፣ እውነትን ተፃራሪ ከመሆን፣ ከንፍቅና፣ ከይስሙልኝ፣ ከይዩልኝ ባንተ እጠበቃለሁ። ከደንቆሮነት፣ ከዲዳነት፣ ከእብደት፣ ከቁምጥና፣ ከለምጥና ከመጥፎ በሽታዎችም ባንተ እጠበቃለሁ።"[106]

94 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልፈቅሪ፣ (ወልፋቀቲ)፣ ወልቂለቲ፣ ወዝዚለህ። ወአዑዙ ቢከ ሚን አን አዝሊመ አው ኡዝለም።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከድህነት፣ ከችግር፣ ከነገሮች ማነስ፣ ከውርደት ባንተ እጠበቃለሁ። ሌሎችን ከመበደል ወይም በሌሎች ከመበደል ባንተ እጠበቃለሁ።"[107]

95 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ጃሪስሱኢ ፊ ዳሪል ሙቃመቲ ፈኢነ ጃረል ባዲየቲ የተሐወል።" ትርጉሙም "አላህ

---

[106] ነሳኢ በቁጥር 5493፣ ሐኪም በ1/530 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" ውስጥ በ1/406 እና በ "ኢርዋኡል ኽሊል" ቁጥር 852 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[107] አቡዳውድ በቁጥር 1544፣ ነሳኢ በቁጥር 5475 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ አንነሳኢ" 3/1111፣ በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" 1/407 ሶሒሕ ብለውታል። በቅንፉ መሀል ያለው ኢብኑ ሒባን ውስጥ ያለ ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ መዋሪዱዝ-ዞምአን" 2/455 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ሆይ! እኔ በዘውትር መኖሪያ ቤቴ ላይ ከሚገኝ መጥፎ ጎረቤት ባንተ እጠበቃለሁ። የውጪ ጎረቤት የሚወገድ ነውና።"[108]

96 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ቀልቢን ላየኽሸዕ፣ ወሚን ዱዓኢን ላዩስመዕ፣ ወሚን ነፍሲን ላተሽበዕ፣ ወሚን ዒልሚን ላየንፈዕ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሀኡላኢል አርበዕ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከማይተናነስ ቀልብ፣ ተሰሚነት ከሌለው ዱዓእ፣ ከማትጠግብ ነፍስ፣ ከማይጠቅም እውቀት ባንተ እጠበቃለሁ። ከነዚህ አራት ነገሮች ባንተ እጠበቃለሁ። "[109]

97 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን የውሚስ-ሱኢ፣ ወሚን ለይለቲስ-ሱኢ፣ ወሚን ሳዐቲስ-ሱኢ፣ ወሚን ሷሒቢስ-ሱኢ፣ ወሚን ጃሪስ-ሱኢ ፊ ዳሪል ሙቃመህ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ እኔ ከመጥፎ ቀን፣ ከመጥፎ ምሽት፣ ከመጥፎ ሰአት፣ ከመጥፎ

---

[108] ቡኻሪ በ "አደቡል ሙፍረድ" ውስጥ ቁጥር 117 ላይ፣ ሐኪም በ1/532 የዘገቡት ሲሆን ሶሒሕም ብሎታል። ዘሀቢም ተስማምተውበታል። ነሳኢም በቁጥር 5517 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሑል ጃሚዕ" 1/408 ላይ እና በ "ሶሒሕ አንነሳኢ" 3/1118 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[109] ቲርሚዚ በቁጥር 3482፣ አቡዳውድ በቁጥር 1549 የዘገቡት ሲሆን ታላቁ ሊቅ አልባኒም በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" ውስጥ በቁጥር 1295 እና በ "ሶሒሕ ነሳኢ" 3/1113 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ጓደኛ፣ በዘውትር መኖሪያ ቤቴ ላይ ካለ መጥፎ ጎረቤት ባንተ እጠበቃለሁ።"[110]

98 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከል ጀነተ ወአስተጂሩ ቢከ ሚነንናር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ጀነትን እጠይቅሃለሁ። ከእሳትም ባንተ እጠበቃለሁ።" (ሶስት ጊዜ)[111]

99 -"አላሁመ ፈቅቂህኒ ፊድ-ዲን" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ሀይማኖቴን አስገንዝበኝ።"[112]

---

110 ጦበራኒ የዘገቡት ሲሆን ሀይሠሚ በ "ዘዋኢድ" ውስጥ በ10/144 ላይ "ሰነዱ ላይ ያሉ ሰዎች የሶሒሕ ዘጋቢዎች ናቸው።" ብለዋል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልጃሚዕ" ውስጥ በ/411 በቁጥር 1290 ላይ ሐሰን ብለውታል።

111 ቲርሚዚ በቁጥር 2572፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3340፣ ነሳኢ በቁጥር 5536 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ቲርሚዚ" 2/319፣ በ "ሶሒሕ ነሳኢ" 3/1121 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። የነሳኢ ዘገባም "ጀነትን ሶስት ጊዜ ከአሏህ የጠየቀ ጀነት 'አላህ ሆይ! ጀነት አስገባው።' ትልለታለች።ከእሳት ሶስት ጊዜ በአሏህ የተጠበቀም እሳት 'አላህ ሆይ! ከእሳት ጠብቀው።' ትልለታለች።" የሚል ነው።

112 ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለኢብኑ ዓባስ አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና ስላደረጉት ዱዓ ቡኻሪይ እና ሙስሊም ያወሩት ዘገባ ይህንን ዱዓእ ይጠቁማል። ቡኻሪ በቁጥር 143፣ ሙስሊም በቁጥር 2477 ዘግበውታል።

100 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ አን ኡሽሪከ ቢከ ወአነ አዕለም፤ ወአስተግፊሩከ ሊማ ላ አዕለም።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እያወቅኩኝ ባንተ ላይ ከማጋራት ባንተ እጠበቃለሁ፤ ለማላውቀው ደግሞ ምህረትህን እጠይቅሀለሁ።"[113]

101 -"አላሁመ ኢንፈዕኒ ቢማ ዐለምተኒ ወዐሊምኒ ማ የንፈዑኒ ወዚድኒ ዒልማ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ባሳወቅከኝ ጥቀመኝ፣ የሚጠቅመኝንም አሳውቀኝ፣ እውቀትንም ጨምርልኝ።"[114]

[115]"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ዒልመን ናፊዐን፣ ወሪዝቀን ጦዪበን፣ ወዐመለን ሙተቀበላ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ!

---

[113] አሕመድ 4/403 ላይ፣ ኢብኑ አቢ ሸይባ 10/337 ላይ፣ ጦበራኒ በ "ሙዕጀሙል አውሰጥ" 4/284 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ "ሶሒሕ ተርኺብ ወትተርሂብ" 1/19 ላይ ሐሰን ብለውታል።

[114] ቲርሚዚ በቁጥር 3599፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 259 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ" 1/47 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[115] ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 925፣ ነሳኢ "ዐመሉል የውሚ ወልለይለህ" በሚለው መፅሀፋቸው ውስጥ በቁጥር 102፣ አሕመድ 6/294 እና 305 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ 1/152 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ጠቃሚ እውቀትን፣ መልካም ሲሳይን፣ ተቀባይነት ያለው ስራን እጠይቅሀለሁ።"

103 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ያ አላሁ ቢአነከል ዋሒዱ አልአሐዱ አስሰመዱ አለዚ ለምየሊድ ወለም ዩለድ ወለም የኩን ለሁ ኩፉወን አሐድ አን ተቿፊረ ሊ ዙኑቢ ኢነከ አንተ አልቿፉሩ አርረሒም።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! አንተ አንድ፣ ብቸኛ፣ መጠጊያ፣ ያ የማይወልድ፣ የማይወለድ፣ ለርሱ አንድም ቢጤ የሌለው ነህ። አላህ ሆይ! ለኔ ወንጀሎቼን እንድትምር እጠይቅሀለሁ። እነሆ አንተ እጅግ መሀሪና እጅግ አዛኝ ነህና።"[116]

104 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ቢአነ ለከል ሐምደ፤ ላኢላሀ ኢላ አንተ (ወሕደከ ላሸሪከ ለክ) አልመናኑ ፣ (ያ) በዲዑስ-ሰማዋቲ ወልአርዷ፣ ያዘልጀላሊ ወልኢክራም፣ ያ ሐዩ ያ ቀይዩም ኢኒ አስአሉከ (አልጀነተ ወአዑዙ ቢከ ሚነናር)" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ እጠይቅሀለሁ ላንተ ምስጋና የተገባህ ነህ፤ ከአንተ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም። (ብቸኛ ነህ

---

[116] ነሳኢ በቁጥር 1300 የሐዲሱ ቃላትም የሳቸው ዘገባ ነው። ፣ ነሳኢ በ "አልኩብራ" ቁጥር 7665 ላይ፣ አቡዳውድ በቁጥር 985 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ሱነን አንነሳኢ" 1/147 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ላንተም አጋር የለህም።) ፤ ለጋሽ የሆንክ ፤ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆነከው (ሆይ)፤ የግርማና ክብር ባለቤት የሆንከው ሆይ! ፤ ህያውና በራሱ የቆመ የሆንከው ሆይ! እኔ (ጀነትን) እጠይቅሀለሁ። (ከእሳትም ባንተ እጠበቃለሁ።)[117]

105 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ቢአኒ አሽሀዱ አንነከ አንተል-ሏሁ ላኢላሀ ኢላ አንተ አልአሐዱ አስሶመዱል-ለዚ ለምየሊድ ወለምዩለድ ወለምየኩን ለሁ ኩፉወን አሐድ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እነሆ አንተ አላህ መሆንክንና ከአንተም በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ፣ ብቸኛ፣ መጠጊያ፣ ያ ያልወለደና ያልተወለደ ፣ ለርሱ አንድም ቢጤ የሌለው መሆንክን እመሰክራለሁ።"[118]

---

[117] አቡዳውድ በቁጥር 1495፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3858፣ ነሳኢ በቁጥር 1299፣ ቲርሚዚ በቁጥር 3544 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ"ሶሒሕ አንነሳኢ" 1/279 እና በ "ሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ" 2/329 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[118] አቡዳውድ በቁጥር 985፣ ቲርሚዚ በቁጥር 3475፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3857 ፣ አሕመድ 5/360 ላይ የዘቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ሱነን አትቲርሚዚ" 3/163 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

106 -"ረቢሻፊርሊ ወቱብ ዐለየ፤ ኢንነከ አንተ-ትተዋቡል ኻፉር" ትርጉሙም "ጌታዬ ማረኝ! ተውባዬን ተቀበለኝ፤ እነሆ አንተ ተመላሾችን የምትቀበልና መሀሪ ነህና።"[119]

107 -"አላሁመ ቢዒልሚከል ኻይበ፣ ወቁድረቲከ ዐለል ኸልቂ አሕዪኒ ማ ዐሊምተል ሐያተ ኸይረን ሊ፤ ወተወፍፊኒ ኢዛ ዐሊምተል ወፋተ ኸይረን ሊ፤ አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸሽየተከ ፊልኻይቢ ወሽሸሀደህ፤ ወአስአሉከ ከሊመተል ሐቂ ፊርሪዷ ወልኻዶብ፤ ወአስአሉከል ቀስደ ፊልጊና ወልፈቅር፤ ወአስአሉከ ነዒመን ላ የንፈድ፤ ወአስአሉከ ቁረተ ዐይኒን ላ ተንቀጢዕ፤ ወአስአሉከ-ርሪዷ በዕደል ቀዷእ፤ ወአስአሉከ በርደል ዐይሺ በዕደል መውት፤ ወአስአሉከ ለዝዘተ-ንነዞሪ ኢላ ወጅሂክ፤ ወሽሸውቀ ኢላ ሊቃኢከ ፊ ኻይሪ ዶርራአ ሙዷረቲን ወላ ፊትነቲን ሙዲለህ፤ አላሁመ ዘይንና ቢዚነቲል ኢማኒ ወጅዐልና ሁዳተን ሙህተዲን።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በሩቅ እውቀትክ፣ በፍጡራን ላይ ባለህ ችሎታክ ህይወት ለኔ

---

119 አቡዳውድ በቁጥር 1518፣ ቲርሚዚ በቁጥር 3434፣ ነሳኢ "አልኩብራ" ውስጥ በቁጥር 10292፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3814 የዘገቡት ሲሆን ከላይ የተጠቀሰው ቃል የቲርሚዚ ዘገባ ነው። አልባኒም በ "ሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ" 2/321 እና በ "ሶሒሕ ቲርሚዚ" 3/153 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

መልካም መሆኗን ካወቅክ እንድታኖረኝ፤ ሞት ለኔ መልካም መሆኗን ካወቅክ እንድትገድለኝ እማፀንሀለሁ። አላህ ሆይ! እኔ በሩቅም በቅርብም ፍራቻህን እጠይቅሀለሁ፤ በውዴታም ሆነ በቁጣ ወቅት እውነት መናገርን እጠይቅሀለሁ፤ በሀብትም ሆነ በድህነት ውስጥ ሚዛናዊነትን እጠይቅሀለሁ፤ የማይጠፋ ፀጋን እጠይቅሀለሁ፤ የማይቋረጥ የአይን ማረፊያን እጠይቅሀለሁ፤ ከውሳኔ በኋላ መውደድን እጠይቅሀለሁ፤ ከሞት በኋላ ያማረ ኑሮን እጠይቅሀለሁ፤ ወደ ፊትህ የመመልከትን እርካታ፣ ያለምንም ጎጂ ጉዳትና አጥማሚ ፈተና አንተን የመገናኘትን ናፍቆት እንድትሰጠኝ እጠይቅሀለሁ፤ አላህ ሆይ በኢማን ጌጥ አስውበን፤ የተመሩ ቅኖችም አድርገን።"[120]

108 -"አላሁመርዙቅኒ ሑበክ፣ ወሑበ መን የንፈዑኒ ሑበሁ ዒንደክ፤ አላሁመ ማ ረዘቅተኒ ሚማ ኡሒቡ ፈጅዐልሁ ቁወተን ሊ ፊማ ቱሒብ፤ አላሁመ ማ ዘወይተ ዐንኒ ሚማ ኡሒቡ ፈጅዐልሁ ፈራኘን ሊ ፊማ ቱሒብ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ውዴታህን፣ እሱን መውደድ አንተ ዘንድ የሚጠቅመኝ የሆነ መውደድን ለግሰኝ፤ አላህ ሆይ! እኔ ከምወዳቸው ነገሮች

---

[120] ነሳኢ በቁጥር 1305 ፣ አሕመድ 4/264 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ነሳኢ" 1/280 እና 1/281 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

መካከል የለገስከኝን አንተ በምትወዳቸው ነገሮች ላይ ሀይል አድርግልኝ፤ አላህ ሆይ! እኔ ከምወዳቸው ነገሮች መካከል ከኔ ላይ ያራቅከውን (ያልሰጠኸኝን) ነገር (እሱን አለማግኘቴ) አንተ በምትወደው ነገር ላይ እንዳተኩር የምታገዝበት አድርገው። "[121]

109 -"አላሁመ ጦህሂርኒ ሚነዝዙኑቢ ወልኸጧያ፤ አላሁመ ነቅቂኒ ሚንሀ ከማ ዩነቅቀ-ሠሠውቡል አብየድ ሚነ-ድደነስ፤ አላሁመ ጦህሂርኒ ቢሠሠልጂ ወልበረዲ ወልማኢል ባሪድ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ከወንጀሎችና ከሀጢአቶች አፅዳኝ፤ አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚጠራው እኔንም ከወንጀል አጥራኝ፤ አላህ ሆይ! በጤዛ፣ በበረዶና በቀዝቃዛ ውሀ አጥራኝ።"[122]

110 -"አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ቡኽሊ ወልጁብኒ ወሱኢል ዑሙሪ ወፊትነቲ -ስሶድሪ ወዐዛቢል ቀብር"

---

[121] ቲርሚዚ በቁጥር 3491 የዘገቡት ሲሆን ሐሰንም ብለውታል። ሸይኽ ዐብዱል ቃድር አልአርነኡጥም "ቲርሚዚም እንዳሉት ሐሰን ነው።" ብለዋል። የሳቸው "ጃሚዑል ኡሱል" የሚለውን ጥንቅራቸው 4/341 ላይ ተመልከት።

[122] ሙስሊም በቁጥር 476፣ ነሳኢ በቁጥር 400 ዘግበውታል።

ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከስስት፣ ከፈሪነት፣ ከመጥፎ እድሜ፣ ከልብ ፈተናና ከቀብር ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ።"[123]

111 -"አላሁመ ረብበ ጂብራኢለ ወሚካኢለ ወረበ ኢስራፊለ አዑዙ ቢከ ሚን ሐረሪ-ንናሪ ወሚን ዐዛቢል ቀብር።" ትርጉሙም "የጂብራኢል የሚካኢል ጌታ፣ የኢስራፊል ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ! ከእሳት ሀሩርነትና ከቀብር ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ።"[124]

112 -"አላሁመ አልሂምኒ ሩሽዲ ወአዒዝኒ ሚን ሸርሪ ነፍሲ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ቅናቻን በውስጤ አስርፅብኝ ከነፍሴ ክፋትም ጠብቀኝ።"[125]

---

[123] ነሳኢ በቁጥር 5469 ላይ የዘገቡት ሲሆን ቃሉም "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከአምስት ነገሮች ይጠበቁ ነበር። ከስስት፣ ከፈሪነት፣ ከመጥፎ እድሜ፣ ከልብ ፈተናና ከቀብር ቅጣት።" የሚል ነው። አቡዳውድም በቁጥር 1539 ዘግበውት አልአርነኡጥ "ጃሚዑል ኡሱል"ን "ተኽሪጅ" ባደረጉበት የግርጌ ማስታወሻቸው 4/363 ላይ ሐሰን ብለውታል።

[124] ነሳኢ በቁጥር 1344፣ አሕመድ 6/61 ላይ፣ በይሀቂ "አድደዓዋት" ላይ በቁጥር 109 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ሶሒሕ ነሳኢ" 3/1121 ላይ እና በ "ሲልሲለቱል አሐዲሡ-ስሶሒሐህ" ቁጥር 1544 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[125] ቲርሚዚ 5/519 ላይ በቁጥር 3483 የዘገቡት ሲሆን ቃሉም የሳቸው ነው። አሕመድም 23/197 ላይ በቁጥር 19992፣ ሐኪም 1/510 ላይ

113 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ዒልመን ናፊዓ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዒልሚን ላ የንፈዕ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ጠቃሚ እውቀትን እጠይቅሀለሁ፤ ከማይጠቅም እውቀትም በአንተ እጠበቃለሁ።"[126]

114 -"አላሁመ ረበ-ስሰማዋቲ [አስሰብዒ] ወረበል አርዷ ወረበል ዐርሺል ዐዚም፤ ረበና ወረበ ኩለ ሸይኢን፤ ፋሊቀል ሐቢ ወንነዋ፤ ወሙንዚለ-ትተውራቲ ወልኢንጂሊ ወልፉርቃን፤ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ኩሊ ሸይኢን አንተ አኺዙን ቢናሲየቲህ፤ አላሁመ አንተል አውወሉ ፈለይሰ ቀብለከ ሸይኡን፤ ወአንተል አኺሩ ፈለይሰ በዕደከ ሸይእ፤ ወአንተዝዟሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይእ፤ ወአንተል ባጢኑ ፈለይሰ ዱነከ ሸይእ፤ ኢቅዷ ዐንነ-ድደይነ ወአግኒና ሚነል ፈቅር" ትርጉሙም "የሰባቱ ሰማያት

---

በተመሳሳይ መልኩ ዘግበውታል። የሙስነድ አጠናቃሪዎች ስለ አሕመድ ዘገባ 33/197 ላይ እንዲህ ብለዋል (በቡኻሪና ሙስሊም መስፈርት የተዘገበ ሶሒሕ ሐዲሥ ነው።) የቲርሚዚን ዘገባ ግን አልባኒ "ዶዒፍ ቲርሚዚ" ገፅ 379 ላይ ዶዒፍ ብለውታል።

[126] ነሳኢ "አልኩብራ" ውስጥ በቁጥር 7867፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3843 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በሶሒሕ ሱነን ኢብኑ ማጀህ 2/327 ላይ ሐሰን ብለውታል። ኢብኑ ማጀህ ዘገባ ላይ ያለው ቃል "አሏህን ጠቃሚ እውቀት ጠይቁት! ከማይጠቅም እውቀትም በአላህ ተጠበቁ!" የሚል ነው።

ጌታ፣ የምድር ጌታ፣ የታላቁ ዐርሽ ጌታ፣ ጌታችን ፣ የሁሉም ነገር ጌታ የሆንከው፣ ቅንጣትንና የቴምር ፍሬን ፈልቃቂ፣ ተውራትን ኢንጂልንና ፉርቃንን አውራጂ የሆንከው አላህ ሆይ! ከሁሉም አንተ አናቱን የምትይዝ ከሆንከው ነገር ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ፤ አላህ ሆይ! አንተ የመጀመሪያ ነህ ከአንተ በፊት አንዳችም የለም፤ አንተ የመጨረሻ ነህ ከአንተ በኋላ አንዳችም የለም፤ አንተ የበላይ ነህ ከአንተ በላይ አንዳችም የለም፤ አንተ (በእውቀትህ) ቅርብ ነህ እንዳንተ ቅርብ አንዳችም የለም እዳችንን ክፈልልን ከድህነትም አብቃቃን።"[127]

115 -"አላሁመ አልሊፍ በይነ ቁሉቢና ወአስሊሕ ዛተ በይኒና ወህዲና ሱቡለ-ስሰላሚ ወነጅጂና ሚነ-ዝዙሉማቲ ኢለን-ኑሪ ወጀንኒብናል ፈዋሒሽ ማ ዘሀረ ሚንሀ ወማ በጦን፤ ወባሪክ ለና ፊ አስማዒና፣ ወአብሷሪና፣ ወቁሉቢና፣ ወአዝዋጂና፣ ወዙርሪያቲና፤ ወቱብ ዐለይና ኢንነከ አንተ አትተዋቡር-ረሒም፤ ወጅዐልና ሻኪሪነ ሊኒዐሚከ ሙሥኒነ ቢሀ ዐለይከ ቃቢሊነ ለሀ ወአትሚምሀ ዐለይና።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በልቦቻችን መካከል አስተሳስር፣ በመካከላችንም አስተካክል፣ የሰላም

---

[127] ሙስሊም በቁጥር 2713 ከአቡ ሁረይራ አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና ዘግቧል።

መንገድንም ምራን፤ ከጨለማዎች ወደ ብርሀንም አድነን፤ ግልፅ ከሆነም ሆነ ከተደበቀ ፀያፍ ነገሮች አርቀን፤ በመስሚያዎቻችን፣ በአይኖቻችን፣ በልቦቻችን፣ በሚስቶቻችንና በዝርያዎቻችን ለኛ ባርክልን፤ እነሆ አንተ ተመላሾችን ተቀባይ አዛኝ ነህና ፀፀታችንን ተቀበለን፤ ለፀጋዎችህም አመስጋኞች፣ በሚገባት የምናውላትና በርሷ ምክንያት አንተን የምናወድስ አድርገን። አንተም ሙላልን።"[128]

116 -"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸይረል መስአለቲ፣ ወኸይረድ-ዱዓኢ፣ ወኸይረን-ነጃሒ፣ ወኸይረል ዐመሊ፣ ወኸይረሥ-ሠዋቢ፣ ወኸይረል ሐያቲ፣ ወኸይረል መማቲ፣ ወሠብቢትኒ፣ ወሠቅቂል መዋዚኒ፣ ወሐቂቅ ኢማኒ፣ ወርፈዕ ደረጃቲ፣ ወተቀበል ሶላቲ፣ ወኻፊር ኸጢአቲ፣ ወአስአሉከድ-ደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀንነቲ። አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ፈዋቲሐል ኸይሪ፣ ወኸዋቲመሁ፣ ወጀዋሚዐሁ፣ ወአወለሁ፣ ወዟሂረሁ፣ ወባጢነህ ወድደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀንነቲ አሚን" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ መልካሙን ጥያቄ፣ መልካሙን ልመና፣

---

[128] አቡዳውድ ቁጥር 969 ላይ፣ ሐኪም 1/265 ላይ የዘገቡት ሲሆን ቃሉም የሳቸው ነው። እንዲህም ብለዋል (በሙስሊም መስፈርት ሶሒሕ ነው።) ዘሀቢም 1/26 ላይ ተስማምተውበታል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልአደቡል ሙፍረድ" ቁጥር 630 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

መልካሙን ስኬት፣ መልካሙን ስራ፣ መልካሙን ምንዳ፣ መልካሙን ህይወት፣ መልካሙን ሞት እጠይቅሀለሁ። አፅናኝ፣ ሚዛኔንም አክብድ፣ ኢማኔንም አረጋግጥልኝ፤ ደረጃዬንም ከፍ አድርግ፣ ሶላቴንም ተቀበለኝ፣ ወንጀሌንም ማረኝ፣ ከጀነት ከፍ ያለውን ደረጃ እጠይቅሀለሁ። አላህ ሆይ! እኔ የመልካምን መክፈቻዎች፣ መዝጊያዎችና ሰብሳቢዎች፣ መጀመሪያውን፣ ውጫዊውን፣ ውስጣዊውን ከጀነትም ከፍ ያሉትን ደረጃዎች እጠይቅሀለሁ። አሚን"

"አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ኸይረ ማ አቲ፣ ወኸይረ ማ አፍዐል፣ ወኸይረ ማ አዕመል፣ ወኸይረ ማ በጦን፣ ወኸይረ ማ ዘሀር፣ ወድደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀነቲ አሚን። አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አን ተርፈዐ ዚክሪ፣ ወተዶዐ ዊዝሪ፣ ወቱስሊሐ አምሪ፣ ወቱጦህሂረ ቀልቢ፣ ወቱሐስሲነ ፈርጂ፣ ወቱነውዊረ ቀልቢ፣ ወተሻፊረ ሊ ዘንቢ፣ ወአስአሉከ-ድደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀነቲ አሚን። አላሁመ ኢኒ አስአሉከ አን ቱባሪከ ፊ ነፍሲ፣ ወፊ ሰምዒ፣ ወፊ በሶሪ፣ ወፊ ሩሒ፣ ወፊ ኸልቂ፣ ወፊ ኹሉቂ፣ ወፊ አህሊ፣ ወፊ መሕያየ፣ ወፊ መማቲ፣ ወፊ ዐመሊ። ፈተቀበል ሐሰናቲ ወአስአሉከ -ድደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀነቲ አሚን።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከምተገብረው መልካሙን፣ ከምሰራው መልካሙን፣ ከምፈፅመው መልካሙን፣ ከተሰወረው መልካሙን፣ ይፋ ከሆነውም መልካሙን፣

ከጀነትም ከፍ ያሉትን ደረጃዎች እጠይቅሀለሁ። አሚን አላህ ሆይ! እኔ መወሳቴን ከፍ እንድታደርግ፣ ሸክሜን እንድታነሳ፣ ጉዳዬን እንድታስተካክል፣ ልቤን እንድታፀዳ፣ ብልቴን እንድትጠብቀው፣ ቀልቤን እንድታበራ፣ ወንጀሌን እንድትምር እጠይቅሀለሁ። ከጀነትም ከፍ ያሉትን ደረጃዎች እጠይቅሀለሁ። አሚን አላህ ሆይ! እኔ በነፍሴ፣ በመስሚያዬ፣ በአይኔ፣ በህይወቴ፣ በአፈጣጠሬ፣ በባህሪዬ፣ በቤተሰቦቼ፣ በህይወቴ፣ በሞቴ፣ በስራዬ እንድትባርክ እጠይቅሀለሁ። መልካም ስራዬን ተቀበለኝ። ከጀነትም ከፍ ያሉትን ደረጃዎች እጠይቅሀለሁ። አሚን"[129]

117 -"አላሁመ ጀንኒብኒ ሙንከራቲል አኽላቂ፣ ወልአህዋኢ፣ ወልአዕማሊ፣ ወአልአድዋእ።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ከፀያፍ ምግባሮች፣ ከፀያፍ ዝንባሌዎች፣ ከፀያፍ ተግባሮችና በሽታዎች አርቀኝ።"[130]

---

[129] ሐኪም ከኡሙ ሰለማ ወደ ነቢዩ በተጠጋ ሓዲሥ 1/520 ላይ የዘገቡት ሲሆን ሶሒሕም ብለውታል። ዘሀቢም 1/520 ላይ ተስማምተውበታል። በይሀቂም በአድደዐዋት ውስጥ ቁጥር 225 ላይ፣ አጥጦበራኒም "አልከቢር" ውስጥ 23/326 ቁጥር 717 ላይ ዘግበውታል።

[130] ሐኪም 1/523 ላይ የዘገቡት ሲሆን (በሙስሊም መስፈርት መሰረት ሶሒሕ ነው።) ብለውታል። ዘሀቢም 1/532 ተስማምተውበታል።

118 -"አላሁመ ቀንኒዕኒ ቢማ ረዘቅተኒ ወባሪክ ሊ ፊሂ ወኽሉፍ ዐለየ ኩለ ቓኢበቲን ሊ ቢኸይር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በሰጠኸኝ ሲሳይ አብቃቃኝ፣ በርሱም ለኔ ባርክልኝ፣ ከኔ የራቀውንም ሁሉ ለኔ በመልካም ተካልኝ።"[131]

119 -"አላሁመ ሐሲብኒ ሒሳበን የሲራ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ቀላል ሂሳብን ተሳሰበኝ።"[132]

---

አጥጦበራኒም "ሙዕጀሙል ከቢር" ውስጥ 19/19 ላይ በቁጥር 36 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ "ዚላሉል ጀነት" ቁጥር 13 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[131] ሐኪም 1/532 ላይ የዘገቡት ሲሆን ሶሒሕም ብለውታል ዘሀቢም 1/510 ከኢብኑ ዐባስ አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና በተላለፈው ዘገባ ላይ ተስማምተውበታል። በይሀቂም በ "አልአደብ" ውስጥ በቁጥር 1084፣ "አድደዓዋቱል ከቢር" ውስጥም ቁጥር 211 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልሐፊዝ ኢብኑ ሐጀር በ "አልፉቱሐቱ አርረባኒየህ" 4/383 ላይ ሐሰን ብለውታል።

[132] አሕመድ 6/48 ላይ፣ ሐኪም 1/255 ላይ የዘገቡት ሲሆን (በሙስሊም መስፈርት መሰረት ሶሒሕ ነው።) ብለዋል። ዘሀቢም 1/255 ላይ ተስማምተዋል። ዓኢሻ አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና እንዲህ አለች "የተመለሱ ጊዜ የአላህ ነቢይ ሆይ! ቀላል ሂሳብ ምንድነው? አልኳቸው። እሳቸውም 'ወደ መፅሀፉ ታይቶለት ይቅር መባሉ ነው። ዓኢሻ ሆይ! እነሆ የዛን ቀን አላህ በሂሳቡ የተሟገተው ሰው ጠፋ። አማኝ የሚያገኘው መከራ ሁሉ በርሱ አላህ ይምረዋል የምትወጋው እሾክ እንኳ

120 -"አላሁመ አዒንና ዐላ ዚክሪከ፣ ወሹክሪከ፣ ወሑስኒ ዒባደቲክ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! አንተን በማውሳት፣ በማመስገንና አምልኮህን በማሳመር ላይ አግዘን።"[133]

121 -"አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ ኢማነን ላ የርተድ፣ ወነዒመን ላ የንፈድ፣ ወሙራፈቀተ ሙሐመዲን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ፊ አዕላ ጀንነቲል ኹልድ" "አላህ ሆይ! እኔ (ወደ ኩፍር) የማይመለስ ኢማንን፣ የማያልቅ ፀጋን፣ በዘውታሪው ከፍተኛው የጀነት ደረጃ ሙሐመድን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መጎዳኘትን እጠይቅሀለሁ።"[134]

---

ሳትቀር።' አሉ።" በዚህ ሐዲሥ ዙሪያ ታላቁ ሊቅ አልባኒ በሚሽካቱል መሷቢሕ ውስጥ (ሰነዱ ጥሩ ነው።) ብለዋል።

[133] ኢማሙ አሕመድ 2/299 ላይ፣ ሐኪም 1/499 ላይ የዘገቡት ሲሆን ሶሒሕም ብለውታል፤ ዘሀቢም ተስማምተውበታል። እንዳሉትም ነው። አቡዳውድ ላይም በቁጥር 1524፣ ነሳኢ በ "አልኩብራ" ውስጥ በቁጥር 9973 ዘግበውታል። አልባኒም በ "ሶሒሕ አልአደቡል ሙፍረድ" ውስጥ ቁጥር 534 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[134] ኢብኑ ሒባን በቁጥር 2436 604 ገፅ ላይ ኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና የተናገሩት አድርገው (መውቁፍ አድርገው) ሲዘግቡት፣ አሕመድ በሌላ ሰነድ በ/386ና 400 ላይ ፤

122 -"አልላሁመ ቂኒ ሸርረ ነፍሲ፣ ወዕዚም ሊ ዓላ አርሸዲ አምሪ፣ አልላሁመጝፊርሊ ማአስረርቱ፣ ወማአዕለንቱ፣ ወማአኽጦእቱ፣ ወማዐመድቱ፣ ወማዐሊምቱ፣ ወማጀሂልቱ" "አላህ ሆይ! የነፍሴን ክፋት ጠብቀኝ፣ በቀናው ጉዳዬ ላይም ቆራጥነትን ግጠመኝ፣ አላህ ሆይ! የደበቅኩትንም፣ ግልፅ ያወጣሁትንም፣ በስህተት የሰራሁትንም፣ ሆን ብዬ የሰራሁትንም፣ ወንጀልነቱን ከማወቅ ጋር የሰራሁትንም፣ ወንጀልነቱን ሳላውቅ የሰራሁትንም ወንጀሎቼን ማረኝ!"[135]

123 -"አልላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ኻለበቲድደይኒ፣ ወኻለበቲል ዐዱዊ፣ ወሽማተቲል አዕዳእ" "አላህ ሆይ! እኔ በእዳ

---

ነሳኢ 'ዐመሉል የውሚ ወልለይላ' በሚለው ኪታባቸው ውስጥ በቁጥር 869 ዘግበውታል። አልባኒ በ 'ሲልሲለቱ አስሶሒሓህ' ውስጥ በቁጥር 2301... ላይ ሐሰን ብለውታል።

[135] ነሳኢ በ"አልኩብራ" ኪታባቸው 6/246 ላይ በቁጥር 10830፣ ሐኪም 1/510 ዘግበውት ሶሒሕ ሲሉት ዘሀቢም ተስማምተውበታል። አሕመድ በ4/444 አርትኦት ተደርጎ በተዘጋጀው ሙስነድ 33/197 ላይ በቁጥር 19992 ዘግበውታል። ሐፊዝ "ኢሷባ" በሚለው ኪታባቸው ውስጥ ሰነዱ ሶሒሕ ነው ብለዋል። አልባኒ በሪያዱስሷሊሒን የግርጌ ማስታወሻቸው ላይ በሐዲስ ቁጥር 1495 ስር ሶሒሕ ብለውታል።

ከመሸነፍ፣ በጠላት ከመሸነፍና የጠላት ደስታ ምንጭ ከመሆን ባንተ እጠበቃለሁ።"[136]

124 -"አልላሁመሻፊር ሊ፣ ወህዲኒ፣ ወርዙቅኒ፣ ወዓፊኒ፤ አዑዙ ቢላሂ ሚንዷቂል መቃሚ የውመል ቂያማ" "አላህ ሆይ! ማረኝ፣ ምራኝ፣ ሲሳይን ለግሰኝ፣ ጤናዬን ለግሰኝ። የትንሳኤ ቀን ከሚኖር ጠባብ ስፍራም በአላህ እጠበቃለሁ።"[137]

125 -"አላሁመ መትቲዕኒ ቢሰምዒ ወበሶሪ፤ ወጅዐልሁመል ዋሪሠ ሚንኒ፤ ወንሱርኒ ዓላ መንየዝሊሙኒ፤ ወኹዝ ሚንሁ ቢሠእሪ" "አላህ ሆይ! በመስሚያዬ፣ በአይኔ አጣቅመኝ! ሁለቱን አካላቶቼ ከኔ ወራሽ አድርጋቸው። በሚበድለኝ ላይም እርዳኝ። ከርሱ (ከበደለኝም) በቀሌን ያዝልኝ።"[138]

---

[136] ነሳኢ በቁጥር 5475፣ አሕመድ በ2/173 ሲዘግቡት አልባኒ በሶሒሕ አንነሳኢ 3/1113 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[137] ነሳኢ በቁጥር 1617፣ ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 1356 ሲዘግቡት አልባኒ በሶሒሕ ሱነን አንነሳኢይ 1/356 ላይና በሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ 1/226 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[138] ቲርሚዚ በቁጥር 3681፣ ቡኻሪ በ"አደቡል ሙፍረድ" ውስጥ በቁጥር 650፣ ሐኪም በ1/523 ሲዘግቡት ሶሒሕም ብለውታል። ዘሀቢም

126 -"አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ዒሸተን ነቂየህ፣ ወሚተተን ሰዊየህ፣ ወመረደን ኻይረ መኽዚን ወላፋዲሕ።" "አላህ ሆይ! እኔ የፀዳ ኑሮ፣ የተስተካከለ አሟሟት፣ የማያዋርድና የማያጋልጥ መመለሻንም እጠይቅሀለሁ።" [141]

127 -"አልላሁመ ለከል ሐምዱ ኩሉህ፤ አልላሁመ ላቃቢዷ ሊማ በሰጥተ፣ ወላ ባሲጠ ሊማ ቀበድተ፣ ወላሀዲየ ሊመን አድለልተ፣ ወላሙዲለ ሊመን ሀደይት፣ ወላሙዕጢየ ሊማ መነዕተ፣ ወላማኒዐ ሊማ አዕጦይት፣ ወላሙቀርሪበ ሊማባዐድተ፣ ወላሙባዒደ ሊማቀርረብት፣ አላሁመብሱጥ ዐለይና ሚንበረካቲከ፣ ወረሕመቲከ፣ ወፈድሊከ፣ ወሪዝቂክ፤ አላሁመ ኢኒ አስአሉከን-ነዒመል ሙቂም አለዚ ላ የሑሉ ወላ የዙል፣ አልላሁመ ኢኒ አስአሉከን-ነዒመ የውመል ዐይለህ፣ ወልአምነ የውመል ኸውፍ፤ አልላሁመ ኢኒ ዓኢዙን ቢከ ሚን ሸርሪ ማ አዕጦይተና ወሸርሪ ማ መነዕተና፤ አልላሁመ ሐቢብ ኢለይነል ኢማነ ወዘይዪንሁ ፊ ቁሉቢና፣ ወከርሪህ ኢለይነል ኩፍረ ወልፉሱቀ ወልዒስያን፤ ወጅዐልና ሚነር-ራሺዲን፤ አልላሁመ ተወፈና ሙስሊሚነ ወአሕዪና ሙስሊሚነ

---

ተስማምተውበታል። አልባኒም በሶሒሕ አትቲርሚዚ 3/188 ውስጥ ሐሰን ብለውታል።

ወአልሒቅና ቢስኗሊሒነ ኻይረ ኸዛያ ወላመፍቱኒን፤ አልላሁመ ቃቲሊል ከፈረተል-ለዚነ ዩከዝዚቡነ ሩሱለክ ወየሱዱነ ዐን ሰቢሊክ፤ ወጅዐል ዐለይሂም ሪጅዘከ ወዓዛበክ፤ አልላሁመ ቃቲል ከፈረተል-ለዚነ ኡቱልኪታበ ኢላሀል ሐቂ (አሚን)" "አላህ ሆይ! ምስጋና ሁሉ ላንተ ነው። አላህ ሆይ! አንተ የዘረጋኸውን (ሲሳይ) ሰብሳቢ የለም፣ የሰበሰብከውንም (ሲሳይ) የሚዘረጋው የለም፣ ያጠመምከውን ሰው መሪ የለም፣ የመራኸውንም ሰው አጥማሚ የለም፣ ለከለከልከውም ሰጪ የለውም ፣ ለሰጠኸውም ከልካይ የለውም፣ ላራቅከውም አቅራቢ የለውም፣ ላቀረብከውም የሚያርቅ የለውም፤ አላህ ሆይ! በኛ ላይ ከበረከትክ፣ ከእዝነትክ፣ ከችሮታህ፣ ከሲሳይህ ዘርጋልን፤ አላህ ሆይ! እኔ የማይቀየርና የማይወገድ የሆነ ዘውታሪ ፀጋን እጠይቅሀለሁ፤ አላህ ሆይ! እኔ የድህነት ቀን ፀጋንና የፍርሀት ቀን ደህንነትን እጠይቅሀለሁ፤ አላህ ሆይ! እኔ ከሰጠኸን መጥፎ ነገርም ከከለከልከንም መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ፤ አላህ ሆይ! ኢማንን ወደ እኛ አስወድድ፣ በልቦቻችን ውስጥም አጊጠው፤ ክህደትን፣ አመፅንና ወንጀልን እኛ ዘንድ የተጠላ አድርገው፤ ከቀናዎቹም አድርገን፤ አላህ ሆይ! ሙስሊም አድርገህ ግደለንም ሙስሊሞች አድርገህም አኑረን፤ ያልተዋረዱና ያልተፈተኑ አድርገህም ወደ ደጋጎቹ አስጠጋን፤ መልክተኞችህን ያስተባበሉና ከአንተ መንገድ የሚዘጉ የሆኑ

ከሀዲያንን ገዳይ የሆንከው አላህ ሆይ! ቅጣትህንና መአትህን በነርሱ ላይ አድርግ!መፅሀፍ የተሰጡት ከሀዲያንን ግደላቸው አንተ እውነተኛ አምላክ የሆንከው ሆይ! ፀሎታችንን ተቀበል። "[139]

128 -"አልላሁመኛፊር ሊ ወርሐምኒ ወህዲኒ ወዓፊኒ ወርዙቅኒ" "አላህ ሆይ! ማረኝ፣ እዘንልኝ፣ ምራኝ፣ ጤናን ስጠኝ፣ ሲሳይንም ለግሰኝ!"[140]

"...... ወጅቡርኒ ወርፈዕኒ" "...... ጠግነኝ፣ ከፍ አድርገኝ።"[141]

---

[139] አሕመድ በዚሁ ቃል በ3/424ና በ24/246 ላይ በቁጥር 15492 ሲዘግቡት በቅንፉ ውስጥ ያለው ሐኪም በ1/507, በ3/23-24 የዘገቡት ነው። ቡኻሪይ በ"አደቡል ሙፍረድ" ውስጥ በቁጥር 699 ሲዘግቡት አልባኒ ለ"ፊቂሁስ-ሲራ" ባዘጋጁት የግርጌ ማስታወሻ በገፅ 284 ላይና በ"ሶሒሕ አልአደቡል ሙፍረድ" ውስጥ በቁጥር 538 በገፅ 259 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። ሙስነድን ያብጠረጠሩ በ24/246 ሰነዱ ላይ ያሉት ሰዎች ታማኝ ናቸው ብለዋል።

[140] ሙስሊም በቁጥር 2696ና በቁጥር 2697 የዘገቡት ሲሆን በሌላ የሙስሊም ዘገባ (እነዚህ ቃላቶች ላንተ ዱንያህንም አኺራህንም ይሰበስቡልሀል።) የሚል ጭማሪ አለው። በሱነን አቡ ዳውድም በቁጥር 850 ላይ እንዲህ የሚል ጭማሪ አለ (ገጠሬው ዞሮ የሄደ ጊዜ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና "በርግጥም እጆቹን በኸይር ሞላ።" አሉ)።

129 -"አልላሁመ ዚድና ወላ ተንቁስና፤ ወአክሪምና ወላ ቱሂንና፤ ወአዕጢና ወላ ተሕሪምና፤ ወአሢርና ወላ ቱእሢር ዐለይና፤ ወአርዷና ወርዷ ዐንና" "አላህ ሆይ! ጨምርልን አትቀንስብን፤ አክብረን አታዋርደን፤ ለግሰን አትከልክለን፤ (እኛን ከጠላቶቻችን ቅድሚያ) ምረጠን (ጠላቶቻችንን) በኛ ላይ አታስበልጥ፤ (በምትሰጠን ነገሮች ሁሉ) ደስተኛ አድርገን አንተም በኛ ተደሰት።"[142]

130 -"አልላሁመ አሕሰንተ ኸልቂ ፈአሕሲን ኹሉቂ" "አላህ ሆይ! ፍጥረቴን እንዳሳመርከው ስነ-ምግባሬንም አሳምርልኝ። "[143]

---

[141] ቲርሚዚ ቁጥር 284 ላይ፣ ኢብኑ ማጀህ ቁጥር 898 ላይ ይመልከቱ። አልባኒ በሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ 1/148 ላይና በሶሒሕ አትቲርሚዚ 1/90 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

[142] ቲርሚዚይ 5/326 ላይ በቁጥር 3173 ፣ ሐኪም 2/98 ላይ ዘግበው ሶሒሕ ብለውታል። ሸይኽ ዐብዱል ቃድር አልአርነኡጥ "ጃሚዑሉ ኡሱልን" በከለሱበት ስራቸው 11/282 ላይ በቁጥር 8847 ሐሰን ብለውታል።

[143] አሕመድ 6/68 ላይ፣ 155 ላይና 1/403 ላይ፣ ኢብኑ ሒባን በ2423፣ ጦያሊሲ 374 ላይ፣ ሙስነድ አቡ የዕላ በቁጥር 5075 ላይ የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ"ኢርዋኡል ኧሊል" 1/115 ላይ በቁጥር 74 ሶሒሕ ብለውታል።

131 -"አልላሁመ ሠብቢትኒ ወጅዐልኒ ሃዲየን መህዲያ" "አላህ ሆይ! አፅናኝ፣ ወደ ቀና የምመራም የተመራሁም አድርገኝ።"[144]

132 -"አልላሁመ ኢኒ አስአሉከሥ-ሠባተ ፊልአምሪ፣ ወልዐዚመተ ዓለር-ሩሽዲ፣ ወአስአሉከ ሙጂባቲ ረሕመቲከ፣ ወዐዛኢመ መቫፊረቲክ፤ ወአስአሉከ ሹክረ ኒዕመቲከ፣ ወሑስነ ዒባደቲከ፤ ወአስአሉከ ቀልበን ሰሊመን ወሊሳነን ሷዲቃ፤ ወአስአሉከ ሚን ኸይሪ ማ ተዕለም፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማተዕለም፣ ወአስተቫፊሩከ ሊማ ተዕለም ኢነከ አንተ ዓልላሙል ቍዩብ" "አላህ ሆይ! እኔ በጉዳዩ ላይ ፅናትንና በቀናነት ላይ ቆራጥነትን፣ እጠይቅሀለሁ፤ እዝነትህንና ምህረትህን በተጨባጭ የሚያስተርፉ ነገሮችን እጠይቅሀለሁ፤ ለፀጋዎችህ ማመስገንንና አምልኮህን ማሳመርን እጠይቅሀለሁ፤ ንፁህ ቀልብና እውነተኛ ምላስን እጠይቅሀለሁ፤ የምታውቀውን መልካም ነገር እጠይቅሀለሁ፤ ከምታውቀው

---

[144] ይህንን የሚያመላክተን ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለጀሪር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ያደረጉት ዱዓ ነው። ቡኻሪይ ውስጥ ቁጥር 6333 ላይ በተጨማሪ ቁጥር 3020 ላይ፣ 3036 እና ሌሎች ቁጥሮችም ላይ ይመልከቱ።

መጥፎ ነገርም ባንተ እጠበቃለሁ፤ ለምታውቀው (ወንጀሎቼ) ምህረትን እጠይቅሀለሁ። እነሆ አንተ ሩቁን አዋቂ ነህና።"[145]

133 -"አልላሁመ ኢኒ አስአሉከል ፊርደውሰ አዕለል ጀነህ" "አላህ ሆይ! እኔ ከፍተኛዋን ጀነት ፊርደውስን እጠይቅሀለሁ።"[146]

---

[145] አሕመድ 28/338 ላይ በቁጥር 17114 ና 28/356 ላይ በቁጥር 17133 ፣ ቲርሚዚይ በቁጥር 3407፣ ጦበራኒ በ"ሙዕጀሙል ከቢር" ውስጥ በዚሁ ቃል በቁጥር 7135፣ በቁጥር 7157፣ በቁጥር 7175፣ በቁጥር 7176፣ 7177፣ 7178፣ 7179፣ 7180 ዘግበውታል፤ ኢብኑ ሒባንም በሶሒሑ ውስጥ 3/215 ላይ በቁጥር 935፣ 5/310 ላይ በቁጥር 1974 ዘግበውታል፤ ሹዐይብ አልአርነኡጥም በሶሒሕ ኢብኑ ሒባን 5/312 ላይ ሐሰን ብለውታል። የሙስነድ ከላሾች 28/338 ላይ በሰነዱ ሐሰን ብለውታል። አልባኒ በ"ሲልሲለቱል አሓዲሣስ-ሶሒሐ" ሰባተኛ ሙጀለድ ውስጥ ቁጥር 3228፣ በ"ሶሒሕ መዋሪደዝ-ዘምአን" ውስጥ ቁጥር 2416ና 2418 ላይ ጠቅሰው (ሶሒሕ ሊኘይሪህ) ብለውታል።

[146] ... አላህን የጠየቃችሁ ጊዜ ፊርደውስን ጠይቁት። እርሱ ምርጡ ጀነትና ከፍተኛው ጀነት ነው። ከርሱ በላይ ያለው የአርራሕማን ዐርሽ ነው። ከርሱ ነው የጀነት ወንዞች የሚፈልቁት።) ከሚለው የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ንግግር የተወሰደ ነው። ቡኻሪይም በቁጥር 2790ና በቁጥር 7423 ዘግበውታል።

134 -"አልላሁመ ጀድ-ዲዲል ኢማነ ፊ ቀልቢ" "አላህ ሆይ! በልቤ ውስጥ ኢማንን አድስ!"[147]

135 -"አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሶላቲን ላተንፈዕ" "አላህ ሆይ! እኔ ከማይጠቅም ሶላት ባንተ እጠበቃለሁ።"[148]

136 -"አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ጃሪስ-ሱኢ፣ ወሚን ዘውጂን ቱሸይዩቡኒ ቀብለ መሺቢ፣ ወሚን ወለዲን የኩኑ ዐለይየ ረበን፣ ወሚን ማሊን የኩኑ ዐለየ ዐዛበን፣ ወሚን ኸሊሊን ማኪሪን ዐይኑሁ ተራኒ ወቀልቡሁ የርዓኒ ኢንረአ

---

[147] - ይህ የተወሰደው ከዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በተላለፈ ሐዲስ እንዲህ ከሚለው ቃል ነው: "የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: '(ያረጀ ልብስ እንደሚነትበው ኢማን በአንዳችሁ ልብ ውስጥ ይነትባልና አላህ ኢማንን በልባችሁ ውስጥ እንዲያድስ ጠይቁት።)'" ሐኪም 1/4 ላይ ዘግበው ሶሒሕ ብለውታል። ዘሀቢም ተስማምተውበታል። ሀይሠሚ በ"መጅመዑዝ-ዘዋኢድ" 1/52 ውስጥ ዘግበውታል። (ጦበራኒ በ"አልከቢር" ውስጥ ዘግበውታል። "ሰነዱም ሐሰን ነው" ብለዋል።) አልባኒም በ"ሲልሲለቱል አሐዲሢስ-ሶሒሐ" 4/113 ላይ በቁጥር 1585 ሐሰን ብለውታል።

[148] አቡዳውድ በቁጥር 1549 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በሶሒሕ ሱነን አቡዳውድ 1/424 ላይ ሶሒሕ ብለውታል።

ሖሰነተን ደፈነሀ ወኢዛ ረአ ሰይዪአተን አዛዐሀ" "አላህ ሆይ! እኔ ከመጥፎ ጎረቤት፣ የመሸበቻ እድሜዬ ከመሆኑ በፊት ከምታሸብተኝ ሚስት፣ በኔ ላይ ጌታ ከሚሆንብኝ ልጅ፣ በኔ ላይ ቅጣት ከሚሆንብኝ ገንዘብ፣ አይኑ የምታየኝ ልቡ የምትጠባበቀኝ መልካም ሲያይብኝ የሚቀብራት መጥፎ ሲያይብኝ የሚያሰራጬብኝ ከሆነ ተንኮለኛ ጓደኛ ባንተ እጠበቃለሁ።"[149]

137 -"አልላሁመ ላ ቱኽዚኒ የውመል ቂያማ" "አላህ ሆይ! የትንሳኤ ቀን አታዋርደኝ።"[150]

---

[149] ጦበራኒ "አድዱዓእ" ውስጥ 3/1425 ላይ በቁጥር 1339 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በ"ሲልሲለቱል አሐዲሧስ-ሶሒሐ" 7/377 ላይ በቁጥር 3137 "ይህ ሐዲስ ሰነዱ ጥሩ ነው። ሁሉም ሰነዱ ላይ ያሉት ሰዎች "ተህዚብ" ውስጥ የተጠቀሱ ናቸው።...... አልኩኝ።" ብለዋል።

[150] አሕመድ በሙስነድ ውስጥ 29/596 ላይ በቁጥር 18056 የዘገቡት ሲሆን ሙስነድን የከለሱትም "ሰነዱ ሶሒሕ ነው።" ብለዋል። ጦበራኒም በ"ሙዕጀሙል ከቢር" 3/20 ላይ በቁጥር 2524 "አልላሁመ ላ ቱኽዚኒ የውመል ቂያማ ወላ ቱኽዚኒ የውመል በእስ" "አላህ ሆይ! የትንሳኤ ቀን አታዋርደኝ። የጭንቅ ቀን አታዋርደኝ።" በሚል ቃል ዘግበውታል።

138 -"አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከል ሙዓፋተ ፊድ-ዱንያ ወልአኺራ" "አላህ ሆይ! እኔ በዱንያም ሆነ በአኺራ ጤናማነትን እጠይቅሀለሁ።"[151]

139 -"አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዒልሚን ላየንፈዕ፣ ወዐመሊን ላዩርፈዕ፣ ወቀልቢን ላየኽሸዕ፣ ወቀውሊን ላዩስመዕ" "አላህ ሆይ! እኔ ከማይጠቅም እውቀት፣ ወደ አላህ ከማይወጣ ስራ፣ ከማይፈራ ቀልብ፣ ሰሚ ከሌለው ቃል ባንተ እጠበቃለሁ።"[152]

140 -"አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሀምሚ፣ ወልሖዘኒ፣ ወልዐጅዚ፣ ወልከሰሊ፣ ወልቡኽሊ፣ ወልጁብኒ፣ ወዶለዒድ-ደይኒ፣ ወኻለበቲር-ሪጃል" "አላህ ሆይ! እኔ ከጭንቀት፣ ከሀዘን፣ ከመልፈስፈስ፣ ከስንፍና፣ ከስስት፣

---

[151] ኢብኑ ማጀህ በቁጥር 3851 የዘገቡት ሲሆን አልባኒም በሶሒሕ ኢብኑ ማጀህ 3/259 ላይና "ሲልሲለቱል አሐዲሢ-ስሶሒሐ" ላይ በቁጥር 1138 ሶሒሕ ብለውታል።

[152] ኢብኑ ሒባን በቁጥር 2440 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በ"ሶሒሕ መዋሪደዝ-ዘምአን" 2/454 ላይ በቁጥር 2066 ሶሒሕ ብለውታል።

ከፈሪነት፣ ከከባድ እዳና በሰዎች ከመሸነፍ ባንተ እጠበቃለሁ። "[153]

141 -"አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢን-ናር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢል ቀብር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ፊተኒ ማዞሀረ ሚንሀ ወማበጦን፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲድ-ደጃል" "አላህ ሆይ! እኔ ከእሳት ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ፤ ከቀብር ቅጣትም ባንተ እጠበቃለሁ፤ ግልፅ ከሆነም ከተደበቀም ፈተና ባንተ እጠበቃለሁ፣ ከደጃል ፈተናም ባንተ እጠበቃለሁ።"[154]

---

[153] ቡኻሪይ በቁጥር 6363 የዘገቡት ሲሆን አነስ እንዲህ አለ: "የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አገለግል ነበርኩ። ከከፍታ በወረዱ ቁጥር "አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ..." ማለትን ሲያበዙ እሰማቸው ነበርኩ።"

[154] ሙስሊም በቁጥር 2867 ዘግበውታል። በውስጡም "ከእሳት ቅጣት በአላህ ተጠበቁ። ከቀብር ቅጣትም በአላህ ተጠበቁ። ...... " ብሎ ጀምሮ እስከመጨረሻው ተጠቅሷል።

142 -"አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ሸሀደተን ፊ ሰቢሊክ" "አላህ ሆይ! እኔ ባንተ መንገድ ላይ ሰማእትነትን እጠይቅሀለሁ።"[155]

143 -"አልላሁመቫፊር ሊ፤ አልላሁመጅዐልኒ የውመል ቂያመቲ ፈውቀ ከሢረን ሚን ኸልቂከ ሚነን-ናስ፤ አልላሁመቫፊር ሊ ዘንቢ፤ ወአድኺልኒ የውመል ቂያመቲ ሙድኸለን ከሪማ" "አላህ ሆይ! ማረኝ፤ አላህ ሆይ! የትንሳኤ ቀን ከብዙ የሰው ፍጡሮችህ በላይ አድርገኝ፤ አላህ ሆይ! ወንጀሌን ለኔ ማረኝ፤ የትንሳኤ ቀን በተከበረ ስፍራ አስገባኝ። "[156]

---

[155] ሙስሊም በቁጥር 1909 የዘገቡት ሲሆን ይህ ዱዓ "በእውነት አላህን ሰማእትነት እንዲያጎናፅፈው የጠየቀ ሰው ፍራሹ ላይ እንኳ ቢሞት አላህ የሰማእታት ደረጃን ያደርሰዋል።" ከሚለው የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ንግግር የተወሰደ ነው።

[156] ቡኻሪይ በቁጥር 4323፣ ሙስሊም በቁጥር 2498 ዘግበውታል። ይህ ዱዓም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለዑበይድ አቢ ዓሚር ካደረጉት ዱዓና ለአቡ ቡርዳእ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ካደረጉት ዱዓ የተቀነጨበ ነው።

144 -"አልላሁመህዲኒ ፊመን ሀደይት፤ ወዓፊኒ ፊመን ዓፈይት፤ ወተወልለኒ ፊመን ተወልለይት፤ ወባሪክ ሊ ፊማ አዕጦይት፤ ወቂኒ ሸርረ ማቀዶይት፤ ኢንነሁ ላየዚሉ መን ዋለይት፤ ተባረክተ ረበና ወተዓለይት" "አላህ ሆይ! ከመራሀቸው ሰዎች መካከል እኔንም ምራኝ፤ ጤናማነትን ከሰጠሀቸው ሰዎች መካከል ለኔም ጤናማነትን ስጠኝ፤ ከተወዳጃሀቸው ሰዎች መካከል እኔንም ተወዳጀኝ፤ በሰጠኸኝ ነገር ባርክልኝ፤ ከወሰንከው ከመጥፎው ጠብቀኝ፤ እነሆ የተወዳጀኸው ሰው አይዋረድምና፤ ጠራህ ጌታችን ከፍም አልክ!"[157]

145 -"ረቢግፊር ሊ ኸጢአቲ የውመድ-ዲን" "ጌታዬ በፍርዱ ቀን ወንጀሌን ማረኝ።"[158]

---

[157] አሕመድ በሙስነድ ውስጥ 3/249 ላይ በቁጥር 1723 የዘገቡት ሲሆን የሙስነድ ከላሾች በ3/249 "ሰነዱ ሶሒሕ ነው።" ብለዋል። ይህ ዘገባ በሌሎች ዘገባዎች በዊትር ላይ ተገድቦ እንደመጣው ሳይሆን ልቅ ሆኖ የመጣ ነው። በዚህ ዘገባ ላይ አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ ብለዋል: "ይህን ዱዓ ያስተምሩን ነበር። ........."

[158] ሙስሊም በቁጥር 214 ዘግበውታል። "ለነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! በጃሂሊያ ዘመን ኢብኑ ጁድዓን ዝምድናን ይቀጥል ነበር፣ ሚስኪኖችን

146 -"አስተግፊሩሏሀ አልዐዚመል-ለዚ ላኢላሀ ኢላ ሁወል ሐይዩልቀይዩሙ ወአቱቡ ኢለይህ" "ታላቅ የሆነውን፣ ያ ከርሱ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የሌለውን፣ ህያውና በራሱ የቆመ የሆነውን አላህ ምህረት እጠይቃለሁ ወደርሱም እመለሳለሁ።"[159]

147 -"አልላሁመግፊር ሊ ዘንቢ፤ ወአዝሂብ ጘይዞ ቀልቢ፤ ወአዒዝኒ ሚን ሙዷልላቲል ፊተን" "አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ፤ የልቤን ከባድ ንዴትም አስወግድልኝ፤ አጥማሚ ከሆኑ ፈተናዎችም ጠብቀኝ።"[160]

---

ያበላ ነበር። ይህ ስራው ይጠቅመዋልን?' ተብለው ተጠየቁ። እርሳቸውም 'አይጠቅመውም። እርሱ አንድም ቀን ጌታዬ የምንዳ ቀን ወንጀሌን ማረኝ አላለምና።' ብለው መለሱ።"

[159] ቲርሚዚይ በቁጥር 3577 የዘገቡት ሲሆን አልባኒ በሶሒሕ ቲርሚዚ 3/469 ላይ ሶሒሕ ብለውታል። "ይህንን ያለ ከጂሀድ ሸሽቶም ቢሆን እንኳ አላህ ይምረዋል።"

[160] ይህ ዱዓ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና "አልላሁመግፊር ለሃ ዘንበሃ ወአዝሂብ ጘይዞ ቀልቢሃ፤ ወአዒዝሃ ሚን ሙዷልላቲል ፊተን" "አላህ ሆይ! ወንጀሏን ማራት፤ የልቧን ከባድ ንዴት አስወግድላት፤ ከአጥማሚ ፈተናዎችም ጠብቃት።"

ብለው ካደረጉላት ዱዓ የተወሰደ ነው። ኢብኑ ዓሳኪር በሰነዱ በ"አልአርበዒን ፊ መናቂቢ ኡምመሃቲል ሙእሚኒን" ውስጥ በገፅ 85 ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና ዘግቦታል። እንዲህም ብሏል "ይህ ሐዲሥ ሶሒሕና ሐሰን ነው። ከበቂየህ ቢን ወሊድ ሐዲሶች ነው።" ኢብኑ ሱኒይም በተመሳሳይ በ"ዐመሉል የውሚ ወልለይለህ" ውስጥ በቁጥር 457 ዘግበውታል። በሌላ የኢብኑ ሱኒይ ግልባጭ ደግሞ: "ወአጂርኒ ሚነሽ-ሽይጧን" "ከሰይጣንም ጠብቀኝ" የሚለው "ሚን ሙዷልላቲል ፈተን" "ከአጥማሚ ፈተናዎች" በሚለው ቦታ ተተክቶ መጥቷል። የአልባኒ "አድዶዒፋህ" ውስጥ በቁጥር 4207 ላይ ስለ ሐዲሱ ዘገባ ይመልከቱ። ይህንን ሐዲሥ አሕመድ ውስጥ ከኡሙ ሰለማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና በቁጥር 26576 2/44 ላይ በተመሳሳይ የተዘገበ የሚያጠናክረው አለ። ቃሉም: "አሏሁመ ረበ ሙሓመዲን ነቢዪ እሻፊር ሊ ዘንቢ ወአዝሂብ ኻይዞ ቀልቢ ወአጂርኒ ሚን ሙዲላቲል ፈተኒ ማ አሕየይተና" "የነቢዩ ሙሐመድ ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ። የልቤን ከባድ ንዴት አስወግድ። እስካኖርከን ድረስ ከአጥማሚ ፈተናዎች ጠብቀኝ። በይ!" የሚል ነው። ሀይሠሚ በ"መጅመዑዝ-ዘዋኢድ" ውስጥ በ10/27 ሐሰን ብለውታል። ይህ ሐዲሥ ጦበራኒ ዘንድ በ"ሙዕጀሙል ከቢር" 23/338 ላይ በቁጥር 785 "ማ አሕየይተና" "እስካኖርከን ድረስ" ከምትለዋ ውጪ ተዘግቧል። ከኡሙ ሀኒእ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና ይህንን ሐዲስ የሚያጠናክር እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! የምለምንበት የሆነን ዱዓ አስተምሩኝ! እርሳቸውም 'አሏሁመ ሻፊር ሊ ዘንቢ... ' 'አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ!......በይ!' በማለት መለሱላት።" ኸራኢጢ በ"ኢዕቲላሉል ቁሉብ" ውስጥ በቁጥር 52 በ"መሳዊኢል አኽላቅ" በቁጥር 323 ዘግበውታል።

148 -"አልላሁመ አሕዪይኒ ዓላ ሱንነቲ ነቢይዪከ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ወተወፍፈኒ ዓላ ሚልለቲሂ ወአዒዝኒ ሚን ሙዷልላቲል ፊተን" "አላህ ሆይ! በነቢይክ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሱና ላይ አኑረኝ። በርሳቸው መንገድም ላይ ሆኜ ግደለኝ። ከአጥማሚ ፈተናዎችም ጠብቀኝ።"[161]

149 -"አልላሁመሶሊ ዓላ ሙሓመድ ወዓላ አሊ ሙሓመድ ከማ ሶልለይተ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ አሊ ኢብራሂም ኢነከ ሓሚዱን መጂድ ወባሪክ ዓላ ሙሐመዲን ወዓላ አሊ ሙሐመድ ከማ ባረክተ ዓላ ኢብራሂም ወዓላ አሊ ኢብራሂም

---

[161] በይሀቂ በ"አልኩብራ" 5/95 ላይ ከኢብኑ ዑመር ዱዓ እንደሆነ አድርገው ዘግበውታል። ኢብኑል ሙልቂንም በ"በድሩል ሙኒር" 6/309 ላይ ጠቅሰውታል። ከዷያእ በመያዝም "ሰነዱ ጥሩ ነው።" ብሏል። ኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ አላህ ሆይ! እኔ ከፈተና ባንተ እጠበቃለሁ። አይበል። ማንኛውም ሰው በፈተና የተከበበ ነው፤ ምክንያቱም አላህ እንዲህ ይላልና: {ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ ፈተና ናቸው።} [አትተጋቡን:15] ይልቁንም ማንኛችሁም የአሏህን ጥበቃ ሲለምን የአሏህን ጥበቃ የሚለምነው ከአጥማሚ ፈተናዎች ለመጠበቅ ይሁን።" ኢብኑ ጀሪር በተፍሲራቸው 13/475 ላይ በቁጥር 15912 ዘግበውታል። ኢብኑ በጧልም በሶሒሕ ቡኻሪይ ማብራሪያቸው 4/13 ላይ ጠቅሰውታል።

[ፊልዓለሚነ] ኢንነከ ሓሚዱን መጂድ" ትርጉሙም፡ "አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ እንዳወደስክ ሁሉ በሙሀመድና በቤተሰቦቻቸው ላይም ውዳሴህን አውርድ፣ አንተ ምስጉንና የላቅክ አምላክ ነህና። አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቻቸው ላይ በረከትህን እንዳሰፈንክ ሁሉ በሙሓመድና በቤተሰቦቻቸው ላይም በረከትህን አዉርድ። [በአለማቱ ውስጥ] አንተ ምስጉንና የላቅከው አምላክ ነህ።"[162]

ግርማውንና የስልጣኑን ልቅና የሚመጥን ምስጋና የአለማት ጌታ ለሆነው አላህ ይገባው። አላህ ሆይ! በነቢያችን ሙሐመድ ላይ፣ በቤተሰቦቻቸው ላይ፣ በባልደረቦቻቸው ላይ፣ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ በተከታዮቻቸውም ላይ በመልካሙ ውዳሴህንና ሰላምህን አስፍን!

---

[162] ቡኻሪይ በቁጥር 3370 የዘገቡት ሲሆን በቅንፉ ውስጥ ያለው ደግሞ ሙስሊም ውስጥ ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራውን ይውደድለትና - በቁጥር 405 የተዘገበ ነው።

# Index


ከቁርኣንና ሐዲሥ የተውጣጡ ዱዓዎች ....................................4

መቅድም ....................................................................7

የዱዓእ ትሩፋት ..............................................................9

ከቁርኣንና ሐዲሥ የተውጣጡ ዱዓዎች .................................. 19